መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ አክሱማዊ? የዳዊት መዝሙር እንደማስረጃ

The inquiries of Zera Yaqob of Aksum: The Psalter as an evidence

ንጉሥ ካሕሳይ[1]

Nguse Kahsay

አሕጽሮተ ጥናት

ዓለማየሁ ሞገስ የተባሉ ጸሐፊ በ1961 “ሐተታ ዘዘርዐ-ያዕቆብ ኢትዮጵያዊ ፈላስፋ” በሚል ርእስ ለቢኤ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት አሳትመው ነበር። በዓለማየሁ ሞገስ ስራ መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብና የዳዊት መዝሙር ጥብቅ ትስስር እንዳላቸው በማያሻማ መንገድ ቢገለጽም ትስስሩ ግን በሚገባ ተዘርዝሮ የተብራራ አይደለም። ስራው ከመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ኹለቱ ቅጂዎች በአንዱ ብቻ በማትኮር የተጻፈም ነው። ሌላው ደግሞ ስራው የየመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ ሳይኾን አይቀርም ተብሎ የሚታማው ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የዳዊት መዝሙር ዕውቀት ፈጽሞ አይዳስስም። ይኽ ጽሑፍ እነዚኽ ክፍተቶች ለመቅረፍ ሰርተዋል። ለዚኽም ጽሑፉ የዳዊት መዝሙር በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ የተጠቀሰበት መንገድ የኢትዮጵያ ሊቃውንት የዳዊት መዝሙር ንባብ ከሚጠቅሱበት ባህል ጋር ማነጻጸር፣ በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ የሚገኙ የዳዊት መዝሙር ንባቦች የቀረቡበት ዓውድ የኢትዮጵያ መጻሕፍት ፈለግ ተከትሎ እንደኾነ መፈተሽ፣ በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ የሚገኙ የዳዊት መዝሙር ንባቦች ምንጮች ሊኾኑ ከሚችሉ የኢትዮጵያ ጸዋትወ ዜማ ወይም ቅኔ መጻሕፍት ማመሰካከር የመሳሳሉ ዓይነተኛ የጥናት ዘዴዎች ተጠቅመዋል። ከተጠቀሱት ዓይነተኛ የጥናት ዘዴዎች ትንተና በመነሣትም ጽሑፉ በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብና የዳዊት መዝሙር ያለ ትስስር ጥብቅና ጥልቅ እንደኾነ አረጋግጠዋል። ትስስሩም ምዕራፍ በመባል በሚታወቀው የጸዋትወ ዜማ ድርሰት እንደሚመሰረት በዝርዝር ተገልጸዋል። ከጽሑፉ ትንተናዎች ማየት እንደሚቻለው ደግሞ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ የዳዊት መዝሙር ዕውቀት፣ ፍቅር እና ክብር በጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የታወቁ ኹሉም ስራዎች ፈጽመው አይገኙም፤ በሕይወቱ እና የስራ ፍሬዎቹም ጭራሽኑ አይታዩም። እነዚኽ ማስረጃዎች ሲመዘኑ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ አድርጎ መውሰድ ፍጹም አዳጋች ያደርጓል። ይኽ ደግሞ በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ በበቂ መንገድና በሚገባ አጽንዖት የተገለጸውን የዘርዐ-ያዕቆብ ኢትዮጵያዊነት ያጸናል።

ቁልፍ ቃላት:- ሐተታ፣ ዘርዐ-ያዕቆብ፣ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ፣ የዳዊት መዝሙር፣ ምዕራፍ

---

[1] የትግራይ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት:- negusekahsaye@gmail.com

Abstract

The inquiries of Zara Yaeqob (hereafter referred to as the Hateta) is an autobiographical text copied from parchment and sent to Antoine D'Abbadie of France by an Italian monk named Giusto d' Urbino, who lived in Ethiopia from 1847 to 1855. However, the original parchment from which the copy was made has yet to be found. Consequently, the authenticity of the Hateta and the true identity of its author have long been subject to debate. Although the Hateta is presented as an autobiography, it is thoroughly interwoven with Psalm verses from the Psalter. Throughout the Hateta, the Psalter is quoted extensively and referenced in depth to the extent that it is sometimes treated as a Psalter itself. This strong link between the Hateta and the Psalter formed the basis of Alemayohu Moges's pioneering work, Hateta Zara Yaeqob: Ethiopian Philosopher (1968). While Alemoyohu Moges's work was novel in opening an important new line of inquiry, it lacked rigor in demonstrating the supposed textual link between the Hateta and the Psalter. His analysis also relied solely on manuscript Eth. Abb. 215, and he did not address Giusto d' Urbino's potential authorship of the Hateta. This study addressed these gaps by thoroughly exploring the link between the Hateta and the Psalter using both Eth. Abb. 215 and Eth. Abb. 234 manuscripts and examining Giusto d' Urbino's knowledge or use of the Psalter in his scholarly contributions. The analysis revealed that most of the Psalm verses appearing in the Hateta are also found in an Ethiopian book called Me'eraf. In contrary, Giusto d' Urbino's scholarly output do not indicate a comparable depth of knowledge, respect or love for the Psalter or Psalms as that displayed in the Hateta. In light of these evidence, it is reasonable to conclude that the Hateta is uniquely Ethiopian and that its true author hailed from Axum.

Keywords: Hateta, Zara Ya'eqob, Giusto d' Urbino, Psalms, Me'eraf

ክፍል አንድ፤ መግቢያ

የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ ማንነት

ጸሐፍት የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ደራሲ ማንነት አስመልክቶ በሚሰጡት አስተያየት በሾለት ጎራ ይከፈላሉ። አንደኛው ጎራ "የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ደራሲ ኢትዮጵያዊ ነው።" ሲሉ በሌላኛው ጎራ ያሉ ደግሞ "የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ደራሲ ኢትዮጵያዊ አይደለም።" በማለት ይሞግታሉ። (Fasil 2017; Getachew 2017; Sumner 1976; Teshome 2019; ብሩህ 2011)

የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ደራሲ ኢትዮጵያዊ የሚያደርጉት ጸሐፍት በፊናቸው "ዘርዐ-ያዕቆብ ብሔሩ አክሱማዊ ነው። ዘርዐ-ያዕቆብ ብሔሩ አክሱማዊ አይደለም።" በሚል ምክንያት በኹለት ተከፍለው እርስበርሳቸው ይለያያሉ። (Getachew 2017; ጌታቸው 2006፤ ብሩህ 2011)

"የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ደራሲ ኢትዮጵያዊ አይደለም።" የሚሉት ደግሞ "ዘርዐ-ያዕቆብ ብሔሩ ጣልያናዊ ነው።" እና "ዘርዐ-ያዕቆብ ብሔሩ ኢትዮጵያዊ አይደለም።" በሚሉ ኹለት ጎራዎች ይከፋፈላሉ። "የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ደራሲ ጣልያናዊ ነው።" የሚሉት ጸሐፍት የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ስራ ከ1847-1855 እ.ጎ.ዘ.አ. በኢትዮጵያ ይኖር ለነበረ ጆስቶ ዳ ኡርቢኖ የሚባል ጣልያናዊ መነኩሴ ይሰጡታል። (Fasil and Setargew 2019; በእምነት)

"የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ደራሲ ኢትዮጵያዊ አይደለም።" የሚሉት ጸሐፍት መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ በተለያዩ ሰዎች ትብብር የተዘጋጀና በተለያዩ ጊዜያት የተሻሻለ ልበ-ወለድ ታሪክ እንደኾነ ይቆጥራሉ። በተጨማሪ እነዚኽ ጸሐፍት ዘርዐ-ያዕቆብ ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊነት እና ኢትዮጵያውያን ለማጠልሸት እንዲኹም ከነዚኽ ጋር ለተቆራኘ (ሃይማኖታዊ) እሴት ወይም (ፖለቲካዊ) ታሪክ መበረዝ ታልሞ የተጻፈ የፈጠራ ድርሰት የታተመበት የብዕር ስም አድርገው ያስባሉ። በዚኽም የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ደራሲ (በመንፈስ) ኢትዮጵያዊ አይደለም፣ ሊኾን አይችልም፣ ሊኾንም አይገባም ይላሉ። (Wion 2013b; ዳንኤል 2011)

እነዚኽ ክርክሮች ዘርዐ-ያዕቆብና መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ በደንብ እንዲጠኑና እንዲነሱ አስችለዋል። በሌላ ጎኑ ደግሞ ክርክሮቹ ዘርዐ-ያዕቆብ የሚገባው የክብር ቦታ እንዳያገኝ በር ከፍቷል። እንዲኹም ክርክሮቹ መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ የሚያስፈልገው ትኩረት እንዳይሰጠው አድርጓል።

ለአገራችን ሰዎች የሚበጀውና የሚጠቅመው የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ ማንነት ማወቅ ሳይኾን መልእክቱ እርባና ካለው ማድመጥና መለየት ነው። ኾኖም ጸሐፊው በሐሰተኝነት እስከተጠረጠረና በማስመሰል እስከተከሰሰ የጽሑፉ ጭብጥ መልእክት ጆሮ ሰጥቶ የሚሰማው አይገኝም፥ አምኖ የሚቀበለው የለም፥ ልብ ብሎ የሚያስተውለውም አይኖርም። ስለዚኽ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ይዘት ለመረዳት የጸሐፊው ማንነት ማስረዳት የግድ አስፈላጊ ነው።

የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ ማንነት ለመረዳት የተደረጉ ቀደምት ጥናቶች የቋንቋ ዳራ (ፊሎሎጂ) መሰረት ያደረጉ ነበሩ። በቅርብ ጊዜያት እየተደረጉ ያሉ ጥኖቶች ግን ከየመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ የቋንቋ/ቃላት አጻጻፍና አጠቃቀም ሥርዓት ጥናት

ይልቅ ወደ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ታሪካዊ እና ፍልስፍናዊ ዳራ ትንተና ያጋድላሉ (Brooh 2022; Dawit 2012; Fasil 2022; Fasil and Setargew 2019; Graness 2022; Kropp 1992; Lee 2022; Luam 2007; Marenbon 2022; Smith 2022; Srivastava 2022; Teshome 2022; ዳዊት 2019)።

ኾኖም የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ ማንነት ለመረዳት ቋንቋ መሰረት ያደረጉ ጥናቶች ሊያበረክቱት የሚችሉት ሐቅ አኹንም አለ። ከዚኽ እሳቤ በመነሣት ይኽ ጽሑፍ የዓለማየሁ ሞገስ[2] ፈለግ በመከተል መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ከየዳዊት መዝሙር ያለው ትስስር አጥንተዋል። ትስስሩ በማጥናት፣ በማብራትና በመተንተንም የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ እና ጸሐፊው ኢትዮጵያዊነት መርምረዋል (ዓለማየሁ 1961)።

የጥናቱ ዓላማዎች

የዚኽ ጽሑፍ ዋና ዐላማ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ ኢትዮጵያውነት መመርመር ነው። በተጨማሪም የሚከተሉት ንዑሳን ዐላማ ይዘዋል።

- የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብና የዳዊት መዝሙር ትስስር መመርመርና መግለጽ
- በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ኾለቱ ቅጂዎች (ዲ አባዲ 234 እና ዲ አባዲ 215) የሚገኙ የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች ማነጻጸር
- የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ አግኝቶ ለዓለም ያስተዋወቀው ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የዳዊት መዝሙር ዕውቀት በራሱ ስራዎች ውስጥ መዳሰስ

የጥናቱ ዘዴ

ከላይ እንደተገለጸው ይኽ ጽሑፍ መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ከየዳዊት መዝሙር ያለው ትስስር በማጥናት የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ ኢትዮጵያዊነት የሚመረምር ነው። በመኾኑም ጽሑፉ በዋናነት ዐይነታዊ የምርምር ዘዴ ተጠቅመዋል። ይኽ መንገድ ግን በዓለማየሁ ሞገስ እና ክላድ ሳምነር ስራዎች ካልኾነ እስካኹን ብዙ ትኩረት አልተሰጠውም (Sumner 1976; ዓለማየሁ 1961)።

በዓለማየሁ ሞገስ ስራ መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብና የዳዊት መዝሙር ጥብቅ ትስስር እንዳላቸው በማያሻማ መንገድ ተገልጸዋል። በዚኽ ስራ የአምሳሉ አክሊሉ ጽሑፍ[1] በዋቢነት በመጠቀምም የጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የቅኔ ክህሎት በሚገባ ተገምግመዋል። ኾኖም በዓለማየሁ ሞገስ ስራ የተገለጸ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብና የዳዊት

[2] ዓለማየሁ ሞገስ የተባሉ ጸሐፊ በ1961 "ሐተታ ዘዘርዐ-ያዕቆብ ኢትዮጵያዊ ፈላስፋ" በሚል ርእስ ለቢኤ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት አሳትመው ነበር። ይኽ ጽሑፍ የዚኽ ስራ ፈለግ በመከተል ተጠንተዋል።

መዝሙር ጥብቅ ትስስር በሚገባ ተዘርዝሮ የተብራራ አይደለም። ሌላው ደግሞ ስራው ከመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ኹለቱ ቅጂዎች በአንዱ[2] ብቻ በማትኮር የተጻፈ ነው። በተጨማሪ ስራው የጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የዳዊት መዝሙር ዕውቀት ፈጽሞ አልዳሰሰም።

በክላድ ሳምነር ስራ ደግሞ የጁስቶ ዳ ኡርቢኖ አጠቃላይ የሥነ-ጽሑፍ ስራዎች በሰፊው ተዳስሰው ቀርበዋል። በዚኽ ስራ የጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የዳዊት መዝሙርና የቅኔ ዕውቀትም በሚገባ መጠን ተቃኝተዋል። በዚኽ ስራ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ኹለቱ ቅጂዎችም በሰፊው ተነጻጽረዋል። ኾኖም በዓለማዮሁ ሞገስ ስራ የተገለጸው የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብና የዳዊት መዝሙር ጥብቅ ትስስር በዚኽ ስራ በከፊል ተገልብጦ ከመደገሙ ውጪ በደንብ አልተብራራም፤ አዲስ ነገርም አልተጨመረበትም።

እነዚኽ በቀደምት ተመሳሳይ ስራዎች የነበሩ ክፍተቶች ለመሙላት የአኹኑ ጽሑፍ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ኹለቱ ቅጂዎች ከየዳዊት መዝሙር ጋር በማነጻጸር የሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ ኢትዮጵያዊነት መርምረዋል። በተጨማሪም ጽሑፉ በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ የሚታዩ የጸሐፊውን የዳዊት መዝሙር ዕውቀት፣ ፍቅር እና ክብር በጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ሌሎች ስራዎች ተንጸባርቀው እንደኾነ ፈትሸዋል።

የጥናቱ ወሰን

ይኽ ጽሑፍ በ መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ (ዲ አባዲ 215 መጀመሪያው ክፍል ወይም ዲ አባዲ 234) እና የዳዊት መዝሙር መጽሐፍ ያለ ትስስር ተመስርቶ የመጽሐፈ ሐተታ ጸሐፊ ኢትዮጵያዊነት ለመመርመር የተጻፈ ነው። መጽሐፈ ሐተታ ወልደ-ሕይወት ግን በዚኽ ጽሑፍ ዳሰሳ አልተካተተም።

ክፍል ኹለት፤ የጥናቱ ትንተና

መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ከየዳዊት መዝሙር ያለው ትስስር

መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብና የዳዊት መዝሙር[3]

ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ በእጁ ገልብጦ የጻፈው ቅጂ (ዲ አባዲ 234) ለአንቷን ዲ አባዲ በፖስታ ልኮለታል። በዚኽ መጽሐፍ ውስጥ ኡርቢኖ በ28 የካቲት 1853 እ.ጎ.ዘ.አ. ያሰፈረው የእጅ ጽሑፍ ማስታወሻ አለ። ማስታወሻው እንዲኽ ይላል፦

> “የዘርዐ-ያዕቆብ መጽሐፍ በተመለከተ፥ ያገኘኹት በአጋጣሚ ነው፤ አላስተዋልኩትም ነበር። ነገር ግን ከወታደር ልጆች አንዱ ከደምቢያ ዘመቻ

[3] በግልጽ ካልተለዩ በስተቀር በዚኽ ጽሑፍ ያሉ የዳዊት መዝሙር ምዕራፎችና ቁጥሮች በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ እንዳሉት የሰባ ሊቃውንት ቅድ የተከተሉ ናቸው።

> በመመለስ ሳለ የዳዊት መዝሙር መግዛት እፈልግ እንደኾነ ጠየቀኝ (እኚኽ ልጆ የተጠቀማቸው ቃላት ናቸው) ፤ እኔም መጽሐፉ አይቼ፥ ምን እንደኾነ ካወቅኩ በኋላ ገዛሁት።"።

ማስታወሻው እንደሚያስረዳው መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ከየዳዊት መዝሙር ማያያዝ ወይም እንደ የዳዊት መዝሙር መጽሐፍ መቁጠር የቆየ እይታና ልምድ ነው። ይኽ የኾነበት ምክንያት ደግሞ መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ከየዳዊት መዝሙር የተወሰዱ ብዙ ንባቦች/ጥቅሶች በውስጡ አካቶ ስለያዘ ነው (Ethiop_Abb_234; Sumner 1976; Wion 2013; ዓለማየሁ 1961)።

መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ከየዳዊት መዝሙር ያለው ጥብቅ ትስስር

በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ውስጥ ከአምስቱ የኦሪት መጻሕፍት፣ ከሌሎች የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እና ከየሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተወሰዱ ሐሳቦችና ጥቅሶች ይገኛሉ። በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ሌሎች ቅድሳት መጻሕፍትም (በቀጥታ ተገልጸውም ሳይገለጹም) በዋቢነት አገልግለዋል። የዳዊት መዝሙር ግን በተለየ አኳኋን መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብን አስጊጠዋል።

በሰንጠረዥ 2 እና ሰንጠረዥ 2 እንደተመላከተው ከ39 የዳዊት መዝሙር ምዕራፎች የተወሰዱ 60 የሚኾኑ ጥቅሶች በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ አሉ[3]። ከእነዚኽ ጥቅሶች 30% በምዕራፍ 5፣ 13% ደግሞ በምዕራፍ 10 ፣ 13% በምዕራፍ 3 ይገኛሉ። የተቀሩት ግን በሌሎች ምዕራፎች ተጠቅሰዋል (Ethiop_Abb_215)።

በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ከሚገኙ 15+ ምዕራፎች ቀጥተኛ የዳዊት መዝሙር ጥቅስ የማይገኝባቸው ምዕራፍ 2 እና 14 ብቻ ናቸው። ኾኖም ግን የተለያዩ በዳዊት መዝሙር ያሉ አገላለጾችና ሐሳቦች በእነዚኽ ኹለት ምዕራፎችም ጭምር ይታያሉ (Ethiop_Abb_215)።

በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ውስጥ ከቀጥተኛ የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች በተጨማሪ ብዙ የዳዊት መዝሙር አገላለጾችና የቃላት አጠቃቀሞች ይገኛሉ። "ወነቅዐ ኵሉ ሕይወት[4]፥ በቅዱስ ስመ ዚአሁ[5]፥ ወኢይትኄለቍ ዓመቲሁ[6]፥ ፈጣሪየ ይሰምዐኒ ሶበ ጸለይኩ ኀቤሁ[7]፥ ወአልጸቁ እትመንደብ[8]፥ ወጎድግ ሊተ ኀጣውኦየ[9]፥ ጥቀ ሠናይ ግብረ እግዚአብሔር ወዕሙቅ ኅሊናሁ[10]፥ በዘእሴሰይ ፍሬ ጻማየ[11]፥ ወፈደዮሙ እኪተ ህየንተ ሠናይት[12]፥ ወያብዕያ ዲበ ምድር[13]፥ ወይትዋኀጡ በበይናቲሆሙ ከመ ብልዐተ እክል[14]፥ ሕምዘ አርዌ ምድር[15]፣ ምስብዒተ[16]፣ ገበርተ ዓመፃ[17]" በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ከሚገኙ የዳዊት መዝሙር ዝውቱር ቃላት እና አገላለጾች መካከል ተጠቃሾቹ ናቸው።

በተጨማሪ በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ውስጥ መዝሙረ (ዳዊት) ቢያንስ 20 ጊዜ ተጽፈዋል[4]። በእነዚኽ ጽሑፋት ውስጥም ከምዕራፍ 2 እና 14 የተወሰዱ ይገኙባቸዋል። ስለሆነም በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ውስጥ ባሉ ምዕራፎች የዳዊት መዝሙር ሐሳብ የማይገኝበት ምዕራፍ የለም (Sumner 1976; ዓለማየሁ 1961)።

ሰንጠረዥ 1፤ በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ (ዲ አባዲ 215) ያሉ የዳዊት መዝሙር (ዕብራይስጥ ቅጂ) ጥቅሶች ብዛት

ምዕራፍ (ዲ አባዲ 215)	የዳዊት መዝሙር (ዕብራይስጥ ቅጂ) ጥቅሶች ብዛት በክፍል					የዳዊት መዝሙር (ዕብራይስጥ ቅጂ) ጥቅሶች ብዛት
	1	2	3	4	5	
1	1	1				2
3	1	1	3	1	2	8
4					4	4
5	1					1
6					1	1
7	4	1				5
8					1	1
9	6	4	1		7	18
10	3	3		2		8
11	1		1		1	3
12	3				1	4
13	2					2
15		1				1
16	1				1	2
ጠቅላላ	23	11	5	3	18	60

የዳዊት መዝሙር (ዕብራይስጥ ቅጂ) በአምስት ክፍል እንደሚመደብ ይታወቃል[5]። በሰንጠረዥ 1 እንደተመላከተው በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ያሉ ጥቅሶች ከዚኽ

[4] 8 ጊዜ መዝሙረ ዳዊት (7 ጊዜ በቀጥታ እና 1 ጊዜ በተዘዋዋሪ)፣ 1 ጊዜ መዝሙረ፣ 3 ጊዜ መዝሙር፣ 8 ጊዜ ዳዊት በሚል ተጽፎ ይገኛል።

[5] ምዕራፍ 1-41 በክፍል 1፣ ምዕራፍ 42-72 በክፍል 2፣ ምዕራፍ 73-89 በክፍል 3፣ ምዕራፍ 90-106 በክፍል 4 ሲመደቡ የተቀሩት ምዕራፎች ደግሞ በክፍል 5 ይቆጠራሉ። ይኽ አከፋፈል በመዝሙረ ክርስቶስ (BL Or. 534፣ EMML 3996) ላይ ተጠቅሶ ይገኛል። የዚኽ ውዳሴ ጸሐፊ ምንጩ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት አባ አትናቴዎስ መጽሐፍ

አንጻር ሲታዩ 38% ከክፍል 1፣ 30% ከክፍል 5፣ 18% ከክፍል 2፣ 8% ከክፍል 3፣ 5% ከክፍል 4 የተወሰዱ ናቸው።በመኾኑም መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ከ39 ምዕራፎች የተወሰዱ ከ60 በላይ የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች/ንባቦች የያዘ ብቻ ሳይኾን ከኹሉም የዳዊት መዝሙር ክፍሎች የተውጣጡ ጥቅሶች/ንባቦችም ያካተተ ነው። የዳዊት መዝሙር በብዛት የሚገኝባቸው የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ምዕራፍ 3፣ 9 እና 10 በተለየ መልኩ ሲታዩ ደግሞ ከኹሉም ክፍሎች የተውጣጡ ጥቅሶች/ንባቦች የያዙ ናቸው ማለት ይቻላል።

ከላይ በተለያየ መልኩ እንደተመላከተው መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ በየዳዊት መዝሙር ንባቦች የተዋበ ነው። ንባቦቹ ግን መጽሐፉ ለማስጌጥ ላይ ላዩ የተጨመሩ ሐሳቦች አይደሉም። ንባቦቹ ከመጽሐፉ ታሪክ ጭብጥ መልዕክት ጋር በጥብቅ የተወሐዱ ናቸው። ይኽም መጽሐፉን የዳዊት መዝሙር እንደ የሕይወት መርህ ተተግብሮ በጥልቀት የተተነተነበት ግለ ታሪክ የሚሰበክበት ዓውድ አድርጎታል። በመኾኑም መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ እንደየዳዊት መዝሙር መጽሐፍ መቆጠሩ የቆየ ልምድ ብቻ ሳይኾን ትርጉም የሚሰጥ አመለካከት ጭምር ነው።

የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊና የዳዊት መዝሙር

ዘርዐ-ያዕቆብ እና የዳዊት መዝሙር ዕውቀቱ

በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ እንደሰፈረው ዘርዐ-ያዕቆብ ከሕጻንነቱ ጀምሮ የዳዊት መዝሙር አንብበዋል[18]። ሊቅ ኾኖ ደግሞ የዳዊት መዝሙር ንባብ አስተምረዋል[19]። ዘርዐ-ያዕቆብ የተማረውና ያስተማረበት የዳዊት መዝሙር በጥናትና ምርምር አትተዋል[20]። ዘርዐ-ያዕቆብ ለጸሎትና ለምስጋና ሌሊትና ቀን የዳዊት መዝሙር ደግመዋል[21]። ዘርዐ-ያዕቆብ ቀለምና ሰሌዳ አዘጋጅቶ የዳዊት መዝሙር ጽፈዋል[22]። በመኾኑም ዘርዐ-ያዕቆብ የዳዊት መዝሙር ተማሪ፣ አስተማሪ፣ ተማራማሪ፣ ዘማሪ (ደጋሚ) እና ጸሐፊ ነበር።

የዘርዐ-ያዕቆብ የዳዊት መዝሙር ፍቅር እና ክብር

ዘርዐ-ያዕቆብ ከልጅነት እስከ ሊቅነት ባደረገው የሐተታ ጉዞ የዳዊት መዝሙር በእጁ ይዞ እንዲኾም በልቦናዉ ስሎ ነበረ። የዳዊት መዝሙር አስተምህሮ ዘርዐ-ያዕቆብ ከዕድገት እስከ ዕለተ ሞት የተከተለው የሕይወት መርህ ነው። በዚኽ ምክንያት ራሱ ደጋግሞ እንደገለጸው ዘርዐ-ያዕቆብ ለየዳዊት መዝሙር የተለየ ፍቅር እና ክብር ነበረው።

ከአይሁድ ጠቢባን የጠቀሰውን ልምድ በማድረግ መዝሙረ ዳዊትን በአምስቱ ሕዋሳት ቁጥርና ምሳሌነት (ርእይ (ማየት)፣ ሰሚዕ (መስማት)፣ አጼንዎ (ማሽተት)፣ ጣዕም (ጣዕም)፣ ገሚሥ (መዳሰስ)) ከፍሎታል። (ጌታቸው 2012)

> “በሙሴ መጻሕፍት ውስጥ ከፈጣሪ ጥበብ ከተፈጥሮ ስርዓትና ሕግ የማይስማማ ይገኛል[23]። እንዲሹም መሐመድ እኔ የማዛችሁ ከእግዚአብሔር ያገኘሁት ነው ይላል። እኛ ግን ትምህርቱ ከእግዚአብሔር ሊኾን እንደማይችል እናውቃለን[24]። … አንዱ ወንድ ብዙ ሴቶችን ያገባ ዘንድ እንደሚገባ በእግዚአብሔር ስም ያስተማረ ትክክል ሊኾን አይችልም፤ ከእግዚአብሔር ዘንድም አይደለም[25]። ዳግመኛም ወንጌል አባትንና እናቱን ሚስቱንና ልጆቹን ያልተወ ለእግዚአብሔር የተዘጋጀ አይደለም ይላል[26]። … ኹሉም የፈጣሪ ስርዓትና የተፈጥሮ ሕግጋትን ያፈርሳል። ስለዚኽ በዚኹ ዓንቀጽ ወንጌል የተናገረው ከእግዚአብሔር የተገኘ ይኾን ዘንድ አይችልም[27]።”

… እያለ ሙሴ፣ መሐመድ እና ወንጌል (አምርሮ) የሚተቸው ዘርዐ-ያዕቆብ የዳዊት መዝሙር ከመንቀፍ ግን አጥብቆ ይታቀባል። (ያሬድ 2007)

ከዚኽ አልፎም “ከየዳዊት መዝሙር ውስጥ ከሕሊናዬ የማይስማማ ባገኝ እኔ እተረጉመዋለሁ፤ ከዕውቀቱ ጋር አስማማዋለሁ። ለእኔም ኹሉ ያምርልኛል[28]።” በማለት ዝንባሌውን ያስረዳል።

> “… በኦሪት ሕግና በክርስቲያን ሕግ በእስላምም ሕግ የቀረው እንዲሁ ብንመራመር ልቡናችን ለእኛ ከሚገልጽልን እውነትና ከፈጣሪ ትክክለኛነት ጋር የማይስማማ ብዙ ይገኛል[29]። … የሃይማኖታቸውን እውነተኛነት ለማስረዳት የምልክቶችና የተአምራት ታሪኮች እየጨመሩ ያጸኑታል። እግዚአብሔር ይኽን አደረገ ይላሉ። እግዚአብሔርን የሐሰት ምስክር ከሐሰተኞችም ተካፋይ ያደርጉታል[30]።” እያለ የተለያዩ ሃይማኖቶች የሚያትተው ዘርዐ-ያዕቆብ የዳዊት መዝሙር ከመተቸት አበክሮ ይታቀባል። ዘርዐ-ያዕቆብ የዳዊት መዝሙርን ከመተቸት የታቀበበት ምክንያት ሲገልጽም “ሰፊ በኾነው ልቡናዬ ኹልጊዜ የዳዊትን መዝሙር እጸልያለሁ፤ ይኽ ጸሎት እጅግ ይጠቅመኛል ሕሊናዬም ወደ እግዚአብሔር ከፍ ከፍ ያደርገዋል[31]።” ይላል። (ያሬድ 2007)

በተጨማሪም ዘርዐ-ያዕቆብ “ያለኝን ሶስት ወቄት ወርቅ የምጸልይበት መጽሐፍና የዳዊት መዝሙር ያዝሁ፤ በሌሊትም ሸሸሁ። የት እንደምኼድም ለማንም አልነገርሁም[32]።” ሲል እንደገለጸው በንጉሥ ሱስንዮስ ዘንድ ነገር ከሚሰሩበት ጠላቶቹ በሸሸ ጊዜ እንኳ ለጸሎት የሚጠቀምበት የዳዊት መዝሙር መጽሐፍ ከእጁ አልለየም። ይኽ ኹሉ ደግሞ ዘርዐ-ያዕቆብ የዳዊት መዝሙር ጉጉ ተማሪ፣ አስተዋይ አስተማሪ፣ ንቁ ተማራማሪ፣ ጽኑ ዘማሪ (ደጋሚ) እና ትጉ ጸሐፊ እንደነበረ ብቻ ሳይኾን ለየዳዊት መዝሙር የተለየ ፍቅር እና አክብሮት ያደረበት እንደነበር በግልጽ ያመለክታል።

የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ቅጂዎችና የዳዊት መዝሙር

የዳዊት መዝሙር በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ኹለቱ ቅጂዎች ያለው ቦታ ተመሳሳይ ነው። ይኹን እንጂ የቅጂዎቹ ንባቦች ሰፊ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ልዩነት ይታይባቸዋል። በኹለቱ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ቅጂዎች ከሚገኙ የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች የቃል አጻጻፍ ልዩነት የሚታይባቸው ንባቦችም አሉ። እነዚኽ ልዩነቶች የታረመ እና ያልታረመ የቃላት አጻጻፍ ልዩነቶች፣ የፊደላት አጻጻፍ ስሕተቶች ወይም ግድፈቶች የፈጠሩዋቸው ናቸው። (ንጉሥ 2016)

በጣም ጥቂት የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች ደግሞ (ከዋናው የዳዊት መዝሙር ንባብ አንጻር) በአንዱ ወይም ኹለቱ ቅጂዎች ተከልሰው ቀርበዋል። ይኽም የንባቦቹ አጻጻፍ ልዩነት እና የቃላት አጻጻፍ ልዩነት አስከትሎዋል። በዚኽ ምክንያት በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ዲ አባዲ 215 ተከልሰው ቢቀርቡም በ ዲ አባዲ 234 ግን ቃል በቃል የተጠቀሱ (ጥቂት) ንባቦች አሉ፤ በተገላቢጦሽም እንዲኹ ነው። ሌላ ደግሞ "ምሕረትከ ይትልወኒ በኵሉ መዋዕልየ ሕይወትየ" የሚል የዳዊት መዝሙር ምዕራፍ 22 ጥቅስ በ ዲ አባዲ 234 ያለ ኾኖ በ ዲ አባዲ 215 ግን የማይገኝ ነው። "ደለወኒ ዘአሕመምከኒ ከመ አእምር ኵነኔከ" የሚል የዳዊት መዝሙር ምዕራፍ 118 ቁጥር 71 ደግሞ በ ዲ አባዲ 215 ኹለት ጊዜ ሲጠቀስ በ ዲ አባዲ 234 ግን አንድ ጊዜ ብቻ ተጠቅሰዋል። ከዚኽ ውጪ ግን በ ዲ አባዲ 215 ያሉ የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች ኹሉ በ ዲ አባዲ 234 አሉ። በመኾኑም የዳዊት መዝሙር በ ዲ አባዲ 234 የተጠቀሰበት እና የተጻፈበት መንገድ ከ ዲ አባዲ 215 የተለየ አይደለም። (Ethiop_Abb_234; Ethiop_Abb_215)

የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ ማንነት

በዚኽ ጽሑፍ የሚከተሉት አምስት ገጽታዎች በሚገባ በማጥናት፣ በማብራትና በመተንተን የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ ኢትዮጵያውነት ለመረዳት ተሰርተዋል።

1. የዳዊት መዝሙር በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ የተጠቀሰበት መንገድ
2. በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ የሚገኙ የዳዊት መዝሙር ንባቦች የቀረቡበት ዓውድ
3. የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ በመጽሐፉ የተገለጸበት ምስል
4. በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ የሚገኙ የዳዊት መዝሙር ንባቦች ምንጮች
5. የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ አግኝቶ ለዓለም ያስተዋወቀው ጆስቶ ዳ ኡርቢኖ የዳዊት መዝሙር ዕውቀ

1. የዳዊት መዝሙር ንባብ በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ የተጠቀሰበት መንገድ

የዳዊት መዝሙር ምዕራፍ በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ውስጥ 4 ጊዜ ተጠቅሰዋል። በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ምዕራፍ 9 "መዝሙር ፱፲ወ፱ አፍቀርኩ እስመ ሰምዓኒ እግዚአብሔር ቃለ ስእለትየ"፣ በምዕራፍ 10 "መዝሙር ፴ ኪያከ ተወከልኩ"፣ በምዕራፍ 12 "መዝሙር ፴ወ፱ ግፍያሙ" እና "መዝሙር ፱ወ፰ እግዚኦ ኢትጸመመኒ" በግልጽ ተጠቅሰዋል። ኹሉም ምዕራፎች የተጠቀሱበት መንገድ ደግሞ የኢትዮጵያ ሊቃውንት የዳዊት መዝሙር ምዕራፍ የሚጠቅሱበት ባህል ተመስርቶና ተከትሎ ነው። ምክንያቱም ኢትዮጵያውያን ጸሐፍት የዳዊት መዝሙር ምዕራፍ የሚጠቅሱት በመለያ ሐረጉ ነው[6]። ይኽ ሐረግም ብዙ ጊዜ በንባቡ መጀመሪያ ይገኛል (ዓለማየሁ 1961፤ ጌታቸው 2006) ።

በመዝሙረ ዳዊት የተነሱት ጭብጦች እና ሃሳቦች በብሉይ ኪዳን ውስጥ ጉልህ ተጽዕኖ አላቸው። ኾኖም በብሉይ ኪዳን ጽሑፎች የሚገኙ ከየዳዊት መዝሙር የተወሰዱ ቀጥተኛ ጥቅሶች ውሱን ናቸው። ከዚኽ በተለየ መልኩ ግን በአዲስ ኪዳን ጽሑፎች ብዙ ከየዳዊት መዝሙር የተወሰዱ ጥቅሶች ይገኛሉ።የማቴዎስ ወንጌል 5፥5[33]፣ የማቴዎስ ወንጌል 13፥35[34]፣ የማቴዎስ ወንጌል 21፥16[35]፣ የማቴዎስ ወንጌል 5፥35[36]፣ የማቴዎስ ወንጌል 22፥44/ወደ ዕብራውያን 1፥13/የሐዋርያት ስራ 2፥34-35[37]፣ የሉቃስ ወንጌል 1፥51[38]፣ የሉቃስ ወንጌል 13፥35[39]፣ የሉቃስ ወንጌል 19፥38[40]፣ የሉቃስ ወንጌል 20፥17[41]፣ የሉቃስ ወንጌል 23፥46[42]፣ የዮሐንስ ወንጌል 2፥17[43]፣ የዮሐንስ ወንጌል 10፥34[44]፣ የዮሐንስ ወንጌል 15፥25[45]፣ የሐዋርያት ስራ 1፥20[46]፣ የሐዋርያት ስራ 2፥25-28[47]፣ የሐዋርያት ስራ 4፥11/የማርቆስ ወንጌል 12፥10/የማቴዎስ ወንጌል 21፥42[48]፣ የሐዋርያት ስራ 4፥25[49]፣ የሐዋርያት ስራ 13፥22[50]፣ ወደ ሮሜ 3፥4[51]፣ ወደ ሮሜ 4፥7[52]፣ ወደ ሮሜ 11፥9-10[53]፣ ወደ ሮሜ 15፥9[54]፣ ወደ ዕብራውያን 1፥5/ወደ ዕብራውያን 5፥5/የሐዋርያት ስራ 13፥33[55]፣ ወደ ዕብራውያን 1፥10-12[56]፣ ወደ ዕብራውያን 2፥6-8[57]፣ ወደ ዕብራውያን 2፥12[58]፣ ወደ ዕብራውያን 3፥7-11[59]፣ ወደ ዕብራውያን 3፥15[60]፣ ወደ ዕብራውያን 4፥7[61]፣ ወደ ዕብራውያን 5፥6[62]፣ ወደ ዕብራውያን 10፥5-7[63]፣ ወደ ዕብራውያን 13፥6[64]፣ 1 ጴጥሮስ 3፥10-12[65]፣ ራእይ 2፥27[66] በአዲስ ኪዳን ጽሑፎች የተጠቀሱ የዳዊት መዝሙር ንባቦች ናቸው። በነዚኽ ንባቦች እንደሚታየው በዛ ዘመን የአዲስና የብሉይ ኪዳን ጽሑፎች መለያ ቁጥር ስላልነበራቸው ይጠቀሱ የነበረው በመልእክታቸው ጭብጥ፣ በጸሐፊያቸው ወይም በመለያ ሐረጋቸው ነበር። በ16ኛው ክፍለ ዘመን የአዲስና የብሉይ ኪዳን ጽሑፎች ተቀባይነት ያለው መለያ ቁጥር ከተበጀላቸው ወዲኽ ደግሞ የዳዊት መዝሙርን ምዕራፍና ቁጥር ተጠቅሞ መጥቀስ ተለምደዋል። በኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስትያን ያሉ ጸሐፍትና ሊቃውንት ግን እስከዛሬ ድረስ የዳዊት መዝሙር ምዕራፍ የሚጠቅሱት በመለያ ሐረጉ ነው።

[6]ይኽ ልማድ በማቴዎስ ወንጌል 27፥46፣ በማርቆስ ወንጌል 15፥34 የተጻፈውን "አምላኬ አምላኬ ለምን ተውኸኝ?" የሚለው የመስቀል ቃል ከየዕብራይስጥ ዳዊት መዝሙር 22፥1 የተመሳጠረበት ትምህርት መሰረት እንዳደረገ ይታመናል።

መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ለዓለም ያስተዋወቀው ጁስቶ ዳ ኡርቢኖም በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ዘንድ የዳዊት መዝሙር 62 “ዘአምላኪየ”፣ የዳዊት መዝሙር ምዕራፍ 3 “ሚበዝሁ” ተብለው እንደሚታወቁ የግዕዝ ቅኔ ባብራራበት መጽሐፉ ገልጦልናል። (Ethiop_Abb_216)

ይኽ የጁስቶ ዳ ኡርቢኖ መጽሐፍ የዳዊት መዝሙር ንባብ በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ የተጠቀሰበት መንገድ የጸሐፊው ወይም የመጽሐፉ ኢትዮጵያውነት በውል እንደማያሳይ ያመላክተናል። በዚኽ ጽሑፍ ለማስረዳት የተፈለገውም የዳዊት መዝሙር ንባብ በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ የተጠቀሰበት መንገድ በኢትዮጵያውን ሊቃውንት ዘንድ የተለመደ እንደኾነ ነው።

2. በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ የሚገኙ የዳዊት መዝሙር ንባቦች የቀረቡበት ዓውድ

አብዛኛዎቹ በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ የሚገኙ የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች በግልጽ ቃል በቃል የተጠቀሱ ናቸው። የተቀሩት ጥቂት ጥቅሶች ግን በጽሑፉ የገቡበት ኹኔታ እንዲስማሙ ተለውጠው ወይም ተስተካክለው ቀርበዋል።

- “ነጽር ላዕሌየ ወተሣሃለኒ። ሀቦ ኃይለ ለገብርከ። ወአድኅኖ ለወልደ አመትከ ግበር <u>ምስሌየ</u> ትእምርቶ ለሠናይ።” የነበረውን “ነጽር ላዕሌየ ወተሣሀለኒ፤ ሀቦ ኀይለ ለገብርከ ወአድኅኖ ለወልደ አመትከ። ግበር <u>ምስሌነ</u> ትእምርተ ለሠናይ” በሚል ተስተካክሎ ተጽፈዋል።
- “ዘኢይትነበብ ኅቡእ ጥበበከ አይዳዕከኒ” የነበረውን “ወኅቡአ ጥበበከ አይድኅኒ” ኾነዋል።
- “ደለወኒ ዘአሕመምከኒ። ከመ አእምር ኵነኔከ።” የሚለውን ንባብ አንዴ “ደለወኒ ዘአሕመምከኒ ከመ አእምር ኵነኔከ” ሌላ ጊዜ ደግሞ “ደለወኒ እግዚኦ ዘአሕመምከኒ። ከመ አእምር ኵነኔከ።” ተብሎ ተጽፈዋል።
- “ዘይነብር ውስተ ሰማይ ይሥሕቆሙ፤ ወእግዚአብሔር ይሳለቅ ላዕሌሆሙ።” የሚለውን በ ዲ አባዲ 215 “ፈጣሪሰ ይስሕቆሙ ወእግዚአ ፍጥረት ይሣለቅ ላዕሌሆሙ።” በ ዲ አባዲ 234 ደግሞ “ፈጣሪሰ ይስሕቆሙ ወእግዚአብሔር ይሣለቅ ላዕሌሆሙ” ተደርጎ ቀርበዋል።
- “እስመ ልዑል እግዚአብሔር ወይራኢ ዘበታሕቱ” የሚለውን በ ዲ አባዲ 215 “እግዚአብሔር ዓቢይ ወልዑል ወይራኢ ዘበታሕቱ” ሲኾን በ ዲ አባዲ 234 ደግሞ “እግዚአብሔር ዓቢይ ወልዑል ውእቱ ወይራኢ ዘታሕተ” ተደርገዋል።
- “ትፈድዮ ለኵሉ በከመ ምግባሩ።” የነበረውን “ዘይፈድዮ ለኵሉ በከመ ምግባሩ።” ኾነዋል።

- “ታሰምዓኒ ትፍሥሕተ ወሐሜተ” አንዴ “ያስምዓነ ትፍሥሕተ ወሐሜተ” ሌላ ጊዜ ደግሞ “አስምዓኒ ትፍሥሕተ ወሐሜተ” ተደርጎ ተጽፈዋል።
- “አብደርኩ እትገደፍ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር ፤ እምእንበር ውስተ ቤተ ኃጥአን።” የሚለውን ታርሞ “እፈቅድ እንበር በሰላም ወበፍቅር ምስለ ኵሉ ሰብእ ወአበድር ፍሬ ፃማየ እሴሰይ። ወእትገደፍ በጎበ ሰብእ ወእንበር ጎቡእ በጥበብ እንተ አለበወኒ እግዚአብሔር እምእንበር ክቡረ ውስተ ቤተ ኃጥአን” በሚል ተስተካክለዋል።
- “ወይሠገሩ በውዴቶሙ እንተ ሐለዩ” የሚል “ኢይሠገሩ በውዴቶሙ ዘገብሩ” በሚል ተተክተዋል።

በእነዚኽ ለውጦች ምክንያት በኹለቱ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ቅጂዎች ጥቂት የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች አጻጻፍ ልዩነቶች አሉ። ቢኾንም የዳዊት መዝሙር በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ የቀረበበት አጠቃላይ ዓውድ ሲታይ የኢትዮጵያ ሊቃውንት እና መጻሕፍት ፈለግ ተከትሎ የተደረገ ነው። የኢትዮጵያ ሊቃውንትና መጻሕፍት የዳዊት መዝሙር በሚጠቅሱበት ጊዜ በግል ወደ እግዚአብሔር በቀጥታ የሚባሉ የዳዊት መዝሙር የልመናና ምስጋና ንባቦች አውጣጥተው በመውሰድ ያጣምርዋቸዋል። ለምሳሌ ገድለ አቡነ ፊልጶስ በተመሳሳይ አኳኋን/ዘይቤ መጻፉ ማየት ይቻላል[7]። (Lee et al. 2024)

በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ያሉ ቀጥተኛ የዳዊት መዝሙር ንባቦች በግል ወደ እግዚአብሔር በቀጥታ የሚደረግ ልመና ወይም ምስጋና ያመዝንባቸዋል። “ነጽር ላዕሌየ ወተሣሃለኒ። ሀቦ ኃይለ ለገብርከ። ወአድኅኖ ለወልደ አመትከ ግበር ምስሌየ ትእምርቶ ለሠናይ።” የነበረውን “ነጽር ላዕሌየ ወተሣሀለኒ፤ ሀቦ ኀይለ ለገብርከ ወአድኅኖ ለወልደ አመትከ። ግበር ምስሌነ ትእምርተ ለሠናይ” በሚል ተተክቶ መጻፉ እንዲኹም “ታሰምዓኒ ትፍሥሕተ ወሐሜተ” የነበረውን “አስምዓኒ ትፍሥሕተ ወሐሜተ” ተደርጎ መጻፉ ደግሞ የየተገለጸው አጻጻፍ ዝንባሌ ገሃድነት ያጠናክራል።

3. የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ በመጽሐፉ የተገለጸበት ምስል

ጌታቸው ኃይሌ “‘በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ሲገናኙ በየዳዊት መዝሙር እንዲዘምሩና የዮሐንስ ወንጌል እንዲያነቡ ሐዋርያት በዲድስቅልያ ደንግገዋል’ የሚለው ነባር ባህል ኹለቱ መጻሕፍት ከኹሉ አስቀድመው በአቢሲንያ ምድር እንዲተረጎሙና ሕጻናትም ፊደል ከለዩ በኋላ ንባባቸውና መሰረታዊ የሃይማኖት ዕውቀታቸው ለማዳበር እንዲውሉ አድርገዋል።” ይላሉ። (ጌታቸው 2006፤ ጌታቸው 2012)

[7] ገድለ አቡነ ፊልጶስ ጻድቅ ወሰማዕት ዘደብረ ሊባኖስ (ገድሉና መልክኡ በግዕዝና በአማርኛ 2013) (ቁጥር 46፣ 54፣ 56፣ 131፣ 217፣ 218 ይመልከቱ።)

በዘመነ ንጉሥ ዓምደ-ጽዮን በነበሩ አቡነ ፊልጶስ ሕይወት ተመስርቶ የተጻፈ ገድል ቁጥር 9 ደግሞ "ወሰዶ አቡሁ ኀበ መምህር ከመ ይትምህር መጻሕፍተ ነቢያት ወሐዋርያት ወመዝሙረ ዳዊት እንዘ ያዐቅብ ቃላቲሆሙ ..." በማለት የዳዊት መዝሙር ትምህርት በኢትዮጵያ ጥንታውነት ይመሰክራል።

እነዚኽ መረጃዎች ከላይ የተመላከተው በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ የሕይወት ታሪክ የሚታይ የዳዊት መዝሙር ትምህርት እና ፍቅር ከተገለጸው ኢትዮጵያዊ ባህል የሚቆራኝ፣ የሚመነጭና የሚስማማ መኾኑ ያስረዳሉ።

4. በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ የሚገኙ የዳዊት መዝሙር ንባቦች ምንጮች

በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ካሉት የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች አብዛኛዎቹ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ባህል እና ልምድ በቃል የሚጠኑ ናቸው። (ዓለማየሁ 1961)

ከታች ባለው ሰንጠረዥ በቁጥር እንደተመላከተው በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ካሉት የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች 60% የሚኾኑት በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ባህል እና ልምድ በቃል እንደሚጠኑና እንደሚቀጸሉ ከሚታወቁ መወድስ፣ መሰተጋብእ፣ ክስተት እና የጾም ምዕራፍ[8] ተብለው በሚጠሩ የምዕራፍ ክፍሎች/ንባቦች ይገኛሉ[9]።

በሰንጠረዡ ከተገለጹ የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች በተጨማሪ በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ያሉ (የዳዊት መዝሙር) አገላለጾች፣ ሐረጎችና ሐሳቦች በምዕራፍ ድርሰትም አሉ። ለምሳሌ "ኢኮነ አምላከ ዘዓመፃ ያፈቅር"[67] በመወድስ፥ የጾም ምዕራፍ እና የምህላ ምዕራፍ፣ "በኵሉ መዋዕለ ሕይወትየ"[68] በመስተጋብእ እና መወድስ ፣ "ጻድቅ በኵሉ ምግባሩ"[69] በየጾም ምዕራፍ እና የምህላ ምዕራፍ ድርሰቶች ይገኛሉ።

[8] ምህላውን ጨምሮ

[9] የማህሌታይ ያሬድ ስራዎች ተብለው የሚታመኑ አምስት ጸዋትው ዜማ ድርሰቶች አሉ። እነሱም ድጉሳ ወይም ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ዝማሬ እና መዋሥዕት ናቸው። ምዕራፍ የሚባል ስራው ከዳዊት መዝሙር ተውጣጥቶ በምዕራፍ በምዕራፍ እየተከፈለ የተደረሰ ትምህርት ነው።
ከላይ እንደተገለጸው የምዕራፍ ትምህርት ዋና መሠረት የዳዊት መዝሙር ነው። በዚኽም ከየዳዊት መዝሙር የተቀዳ (ጾመ) ድጓ ይመሳሰላል። የምዕራፍ ትምህርት አሰጣጥ ግን እንደድጓ ወይም እንደዝማሬና መዋሥዕት መጽሐፍ ዘርግቶ በማንበብ አይደለም። ምዕራፍ በቃል የሚጠናና የሚቀጸል ትምህርት ነው። የምዕራፍ ትምህርት ይዘት ቅደም ተከተልና አወቃቀር ደግሞ ከመጽሐፍ መጽሐፍ ሊለያይ ይችላል። አንዳንዱም የያሬድ ያልኾኑ ድርሰቶችና በምዕራፍ የማይካተቱ ትምህርቶች በአንድ መጽሐፍ ተጠርዘው ይገኛሉ። (በላይ እና መኰንን 2013)፣ (ጥዑመልሳን 1981))

ሰንጠረዥ 2፤ በሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ የሚገኙ የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች እና ከየማህሌታይ ያሬድ ምዕራፍ ትምህርት አንጻር					
	ጥቅስ (ዲ አባዲ 215)	ምዕራፍ (ዲ አባዲ 215)	ምዕራፍ የዜማ ድርሰት	የዳዊት መዝሙር (ሰባ ሊቃውንት)	የዳዊት መዝሙር (ዕብራይስጥ)[70]
1	ንዑ ስምዑኒ እንግርክሙ ኵልክሙ እለ ትፈርህዎ ለእግዚአብሔር መጠነ ገብረ ላቲ ለነፍስየ	1	መወድስ	65፥16	66፥16
2	ወበእግዚአብሔር ትክበር ነፍስየ ይስምዑ የዋሃን ወይትፈሥሑ። እስመ አነ ኃሠሥክዎ ለእግዚአብሔር ወተሰጥወኒ ወይእዜኒ አንትሙኒ ቅረቡ ኀቤሁ ወያበርህ ለክሙ። ወኢይትኃፈር ገጽክሙ። አዕብይዎ ለእግዚአብሔር ምስሌየ። ወናልዕል ስሞ ኀቡረ	1	መስተጋብእ የጸም ምዕራፍ የምህላ ምዕራፍ	33፥2-5	34፥2-5
3	እፎ የአምር እግዚአብሔር ወቦኑ ዘየአምር በአርያም።	3		72፥11	73፥11
4	ወኀቡአ ጥበበከ አይድዓኒ።	3	መወድስ ዋዜማ	50፥6	51፥6
5	አብርሆን ለአዕይንትየ ከመ ኢይኑማ ለመዊት።	3	መስተጋብእ ክስተት የጸም ምዕራፍ የምህላ ምዕራፍ	12፥3	13፥4
6	እደዊከ ገብራኒ ወለሐኒኒ። አለብወኒ ወእትመሀር ትእዛዘከ	3		118፥73	119፥73
7	እስመ ሊተሰ ሕቀ ክመ ዘእምተንተና እገርየ። ወሕቀ ክመ ዘእምድኅፀ ሰኰናየ ወዘንቱሰ ዓማ ውእቱ በቅድሜየ።	3		72፥2/16	73፥2/16
8	ከንቶሁ እንጋ አጽደቅዋ ለልብየ።	3		72፥13	73፥13
9	ዘተከላሁ ለእዝን ኢይሰምዕኑ	3		93፥9	94፥9
10	አንተ እግዚኦ ተአምር ኵሎ ሕሊና ልብየ እምርሑቅ። እስመ ናሁ አንተ አእመርከ ኵሎ ዘቀዳሚ ወዘደኃሪ። ወኵሎ ፍናውየ አንተ አቅደምከ አእምሮ።	3		138፥2-3	139፥2-3
11	እስመ ኵሉ ሰብእ ሐሳዊ ውእቱ	4		115፥2	116፥11
12	ረግዓ ከመ ሐሊብ ልቦሙ	4		118፥70	119፥70
13	ደለወኒ እግዚኦ ዘአሕመምከኒ። ከመ አእምር ኵነኔከ።	4	የጸም ምዕራፍ	118፥71	119፥71
14	ገሥጸኒ አንተ በጽቅ ወተዛለፈኒ በምሕረት። ወቅብዓ ኃጥአንሰ	4	ዋዜማ	140፥5	141፥5

	ወሐሳውያን መምህራን ኢይትቀባዕ ርእስየ				
15	በብርሃንከ እግዚኦ ንርአይ ብርሃነ።	5	መወድስ	35፥9	36፥9
16	ኢገብረ ከማሆሙ ለባዕዳን አሕዛብ ወኢነገሮሙ ፍትሖ	6		147፥9	147፥20
17	ፈጣሪሰ ይስሕቆሙ ወእግዚአ ፍጥረት ይሣለቅ ላዕሌሆሙ።	7	ዋዜማ የጸም ምዕራፍ	2፥4	2፥4
18	እስመ የአምር እግዚአብሔር ገቢረ ፍትሕ ወበግብረ እደዊሁ ተሠግረ ኃጥእ።	7		9፥16	9፥16
	እለ ይነስቱ ሥርዓተ ፈጣሪ ይሠገሩ በግብረ እደዊሁ።	7			
19	ወኵሉ ፍኖቱ ጽድቅ ወርትዕ።	7	መወድስ የጸም ምዕራፍ	24፥10	25፥10
20	ዘይፈድዮ ለኵሉ በከመ ምግባሩ።	7	መስተጋብእ የጸም ምዕራፍ	61፥12	62፥12
21	እግዚአብሔር ዓቢይ ወልዑል ወይራኢ ዘበታሕቱ	8	ዋዜማ	137፥6	138፥6
22	ወመጽአኒ ድንጋፄ ሞት።	9	የጸም ምዕራፍ	54፥4	55፥4
23	መዝሙረ ዘ፱፻፹፱ አፍቀርኩ እስመ ሰምዓኒ እግዚአብሔር ቃለ ስእለትየ።	9	የምህላ ምዕራፍ	114፥1	116፥1
24	ኢይመውት ዘእንበለ ዘአሐዩ። ወእነግር ግብሮ ለእግዚአብሔር።	9	መወድስ	117፥17	118፥17
25	ደለወኒ ዘአሕመምከኒ ከመ አእምር ኵነኔከ	9	የጸም ምዕራፍ	118፥71	119፥71
26	አጽምዓኒ እግዚኦ ጸሎትየ። ወኢትትኃየየኒ ስእለትየ።	9	መስተጋብእ ክስተት የምህላ ምዕራፍ	54፥1	55፥1
27	አድኅነኒ እምትዕግልተ እጓለ እመሕያው	9		118፥134	119፥134
28	አንተ እግዚኦ ኢታርኅቅ ሣህልከ እምኔየ። ምሕረትከ ወጽድቅከ ዘልፉ ይርከባኒ።	9	መስተጋብእ ክስተት መወድስ የጸም ምዕራፍ	39፥11	40፥11
29	ወኢይትኃፈር እግዚኦ እስመ ጸዋዕኩከ።	9		30፥17	31፥17
30	ከመዝ እዜምር ለስምከ ለዓለም። ከመ ተሀበኒ ተምኔትየ ኵሎ ዓሚረ።	9		60፥8	61፥8
31	ነጽር ላዕሌየ ወተሣሃለኒ። ሀቦ ኃይለ ለገብርከ። ወአድኅኖ ለወልደ አመትከ ግበር ምስሌየ ትእምርቶ ለሠናይ።	9	የጸም ምዕራፍ	85፥16-17	86፥16-17
32	በእንተ ስምከ ምርሐኒ ወሴስየኒ።	9	መስተጋብእ	30፥3	31፥3
33	ኢትስሐላ ምስለ ኃጥአን ለነፍስየ	9		27፥3	28፥3


34	ለትኩን ምሕረትከ ላዕሌየ። በከመ ላዕሌከ ተወከልኩ።	9	ክስተት ዋዜማ የምህላ ምዕራፍ	32፥22	33፥22
35	ዘይሰማዕ ግበር ሊተ ምሕረትከ በጽባሕ።	9	መስተጋብእ ክስተት የጸም ምዕራፍ የምህላ ምዕራፍ	142፥8	143፥8
36	ዕቀበኒ ወአብጽኅኒ ዲበ ምድር ወኢታብአኒ ውስተ እደ ጸላእትየ	9	መወድስ	40፥2	41፥2
37	አስምዓኒ ትፍሥሕተ ወሐሤተ	9	ክስተት ዋዜማ	50፥8	51፥8
38	ወኢታስተሐፍረኒ እምተስፋየ	9	መስተጋብእ ክስተት	118፥116	119፥116
39	እመ፡ንቱሰ ይረግሙ አንተ ባርክ። ወያእምሩ ከመ እዴከ ይእቲ ዛቲ	9		108፥27-28	109፥27-28
40	በመዝሙር ዘፀ ኪያከ ተወከልኩ	10	መስተጋብእ ክስተት የጸም ምዕራፍ የምህላ ምዕራፍ	30፥1	31፥1
41	እስመ ኢየአምር ተግባረ እበውዕ በኃይለ እግዚአብሔር	10		70፥15-16	71፥15-16
42	ያስምዓነ ትፍሥሕተ ወሐሤተ	10	ክስተት ዋዜማ	50፥8	51፥8
43	እስመ እግዚአብሔር ያሠርቅ በርሀ ለጻድቃን ወለርቱዓነ ልብ ትፍሥሕተ	10	መስተጋብእ ክስተት የምህላ ምዕራፍ	96፥11	97፥11
44	አስምዓኒ ትፍሥሕተ ወሐሤተ	10	ክስተት ዋዜማ	50፥8	51፥8
45	እግዚኦ ወጥቀ ተሰብሐ ስምከ በኵሉ ምድር	10	የጸም ምዕራፍ የምህላ ምዕራፍ	8፥1-10	8፥1-10
46	አንስ ነዳይ ወምስኪን አነ	10	ክስተት የጸም ምዕራፍ የምህላ ምዕራፍ	39፥17 69፥5 85፥1 108፥22	40፥17 70፥5 86፥1 109፥22
47	ስብሐተ ሐዲሰ።	10	ክስተት መወድስ ዋዜማ የጸም ምዕራፍ	95፥1 97፥1	96፥1 98፥1

			የምህላ ምዕራፍ		
48	እምኀበ እግዚአብሔር ይጸንዕ ሑረቱ ለሰብእ።	11		36፥23	37፥23
49	ምርሐኒ እግዚኦ ፍኖተ እንተ ባቲ አሐውር	11	የጾም ምዕራፍ	142፥8	143፥8
50	እፈቅድ እንበር በሰላም ወበፍቅር ምስለ ኵሉ ሰብእ ወአበድር ፍሬ ፃማየ እሴሰይ። ወእትገደፍ በኀበ ሰብእ ወእንበር ኀቡእ በጥበብ እንተ አለበወኒ እግዚአብሔር አምእንበር ክቡረ ውስተ ቤተ ኃጥአን	11	የምህላ ምዕራፍ	83፥10	84፥10
51	ኢይሠገሩ በውዴቶሙ ዘገብሩ	12		9፥22-23	10፥2
52	ይሠርዎን እግዚአብሔር ለከናፍረ ጕህሉት።	12		11፥3	12፥3
53	በመዝሙር ዘ፴ወ፬ ግፍያሙ	12	የምህላ ምዕራፍ	34፥1	35፥1
54	ወዘያወጽ እግዚኦ ኢትጸመመኒ	12	የምህላ ምዕራፍ	108፥1	109፥1
55	አልቦ ፈሪሃ እግዚአብሔር ቅድመ አዕይንቲሆሙ ወኢያእመርዋ ለፍናተ ሰላም።	13		13፥6	14፥6[10]
56	ኢይትኃፈሩ በመዋዕል እኩያት ወይጸግቡ በመዋዕለ ረኃብ	13		36፥19	37፥19
57	ኢይትአመንዋ ለሐሰት ወኢይሰፈውዋ ለዓመፃ ወኢይሑሩ እምከንቱ ውስተ ከንቱ	15		61፥9-10	62፥9-10
58	ናሁ ከመዝ ይትባረክ ብእሲ ዘይፈርሆ ለእግዚአብሔር	*	ዋዜማ የምህላ ምዕራፍ	127፥4	128፥4
59	እስመ አረጋዊ አነ ጥቀ ወርዘውኩኒ ወረሳእኩ። ጻድቀሰ ዘይትገደፍ ኢርኢኩ። ወዘርኡኒ ኢይዜነስ እክለ። ወውስተ በረከት ይሄሉ ለዓለመ ዓለም	*		36፥25-26	37፥25-26

[10] ይኽ ንባብ በየዕብራይስጡ ቅጂ አይገኝም።


የምዕራፍ ትምህርት የዘውትርና የጾም ምዕራፍ ተብሎ በኹለት ይከፈላል። የዘውትር ምዕራፍ ትምህርት ወቅቱን እየጠበቀ በዓመቱ ውስጥ ባሉት ሳምንታትና በዓላት በአገልግሎት ይውላል። የጾም ምዕራፍ ደግሞ በጾመ አርብዓና በአንዳንድ የምሕላ ቀናት ይነገራል (ጥዑመልሳን 1981፤ በላይ እና መኰንን 2013)።

ከታች ባለው በስእል 1 እና ስእል 2 እንደተመላከተው አብዛኛዎቹ በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ያሉ የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች የተወሰዱት ከጾም ምዕራፍ (ምህላውን ጨምሮ) ነው። ይኽም በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ከተገለጸው የዘርዐ-ያዕቆብ የሕይወት ፈተና በእጅጉ ይቆራኛል። በስእል 2 እንደተመላከተው ከመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ምዕራፍ 11 በኋላ ግን እነዚኽ በጽሞና ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡ ልመና/ምዝጋና ብዙ አናያቸውም። እንደ ዕድል ኾኖ ይኽ ምዕራፍ "ከክርስቶስ ልደት ወዲኽ በ1625 ዓመት ንጉሥ ሱስንዮስ ሞተ። በእርሱ ምትክ ልጁ ፋሲለደስ ነገሠ። እርሱም እንደ አባቱ አስቀድሞ ፈረንጆችን ይወድ ነበር። ነገር ግን ግብጻውያንን አላባረራቸውምና በኢትዮጵያ ባሉት ሃገሮች ኹሉ ሰላም ኾነ። ያን ጊዜ ከዋሻዬ ወጥቼ አስቀድሜ ወደ አማራ አውራጃዎች ኼድኩ።..." እያለ ዘርዐ-ያዕቆብ አምርሮ ከጠላው የብሕትውና ኑሮ የወጣበት ኺደት የሚተርክ ክፍል ነው።



ስእል 1፤ በምዕራፍ ድርሰት የሚገኙ በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ያሉ የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች

በስእል 2 ማየት እንደሚቻለው የጾም ምዕራፍ በብዛት የተጠቀሰበት ክፍል ዘርዐ-ያዕቆብ ለስደትና እንግልት የዳረገውን ከባድ ፈተና በገለጸበት ምዕራፍ 9 ነው። የጾም ምዕራፍ በብዛት የሚገኝባቸው ሌሎች ክፍሎች (ምዕራፍ 7 እና 10) ደግሞ ሰው በኃጢአት ምክንያት ይድንበት ከማይችል ወጥመድ ሲወድቅ፣ ፍጹም የኾነ ጭንቅም ሲደርስበት፣ ከሞት የሚያደርስ ድንጋጤም ሲመጣበት ያን ጊዜ ወደ ድሕነት የሚገኝበት መንገድ ኹሉ የሚያውቅ እግዚአብሔር ተመልሶ እንዲያድነው መጸለይ እንዳለበት የሚመክሩ ናቸው። ይኽም ከኢትዮጵያ (ተዋሕዶ) ቤተ-ክርስቲያን ሊቃውንትና መምህራን ሚመሩት መንፈሳዊ ሕይወት ወይም ኑሮ ሲታይ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ኢትዮጵያውነት በበለጠ ያጸናል።



ስእል 2፤ በየጾም ምዕራፍ (ምህላውን ጨምሮ) ያሉ የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች የሚገኙባቸው የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ (ዲ አባዲ 215) ምዕራፎች

ከላይ የቀረበው የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ኢትዮጵያውነት ማስረጃ በበለጠ ለማስረገጥ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ደራሲ ፈጽሞ ሊኾን የማይችልበት ምክንያት ካለ ማስረዳት ያስፈልጋል። በመኾኑም ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ እንደኾነ ወይም እንዳልኾነ የሚያሳዩ ማብራሪያዎች ቀጥለው ቀርበዋል።

5. ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ እና የዳዊት መዝሙር

ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ (1814-1856 እ.ኃ.ዘ.አ.) ወደ እህቱ፣ ጓደኛው፣ የበላይ ሐላፊዎቹ፣ አንቷን ዲ አባዲ እና (ጥቂት) ሌሎች ሰዎች በርካታ ደብዳቤዎች ልከዋል። በመልእክቶቹ ሊጽፋቸው ያቀደ፣ የጻፋቸው፣ ጽፎአቸው ስላልወደዳቸው ቀዳድዶ ወይ አቃጥሎ ያጠፋቸው፣ የጠፉ(በ)ት መጻሕፍት ወይም ማስታወሻዎች በዝርዝር ገልጸዋቸዋል። ሊተረጉማቸው የሚፈልግ እና የተረጎማቸው መጻሕፍትም እንዲኹ በመልእክቶቹ ተጽፈው ይገኛሉ (Sumner 1976፤ Wion 2012) ።

ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ በኢትዮጵያ ቆይታው የሰበሰባቸው 20[71]+ መጻሕፍት ለአንቷን ዲ አባዲ ልኮለታል። መጻሕፍቱም 17 ነሐሴ 1855 እ.ኃ.ዘ.አ. ለአንቷን ዲ አባዲ በላከለት ደብዳቤ ዘርዝሮ ገልጸዋቸዋል። በ1859 እ.ኃ.ዘ.አ. በታተመው የአንቷን ዲ አባዲ ስብስብ ውስጥም በቁጥር 197-217 እና 234 ተቀምጠዋል (Wion 2012)።

በተገለጸው ደብዳቤ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ራሱ የጻፋቸው አንድ የሰዋስው መጽሐፍ እና ሶስት ትናንሽ የመዝገበ ቃላት መጻሕፍት ለአንቷን ዲ አባዲ እንደላከለት አስፍሯል። Abrege de grammaire ethiopienne, ecrit en Ethiopie, par J.C. d'Urbino, en 1850-1854 የተሰኘ የሰዋስው መጽሐፉ አንቷን ዲ አባዲ በ1859 እ.ኃ.ዘ.አ. ባሳተመው የመጻሕፍት ስብስብ ዲ አባዲ 216 በሚል መለያ ተካቶ በፓሪስ ብሔራዊ ቤተ-መጻሕፍት ይገኛል። Dictionnaire ethiopien francais-amarinna compile en Ethiopie par J.C. d'Urbin, en 1850-55 በሚል ርዕስ የሚታወቀው የመዝገበ ቃላት መጽሐፉ ደግሞ በተመሳሳይ ስብስብ ዲ አባዲ 217 በሚል መለያ ቁጥር በፓሪስ ብሔራዊ ቤተ-መጻሕፍት አለ (D'Abbadie 1859; Ethiop_Abb_216; Ethiop_Abb_217; Wion 2012) ።

ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ አቡን ማስያስ በሚባሉ የበላይ ሐላፊው ትእዛዝ የትርጉም ስራዎች እንዲያከናውን ምክር ተሰጥቶት ይተጋ ነበር። ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የትርጉም ስራዎቹን ሰርቶ በ1852 እ.ኃ.ዘ.አ. ለአቡን ማስያስ እንዳስረከበ ኹለቱ ሰዎች በጻፋዋቸው ደብዳቤዎች ተገልጸዋል። ይኹን እንጂ ስራዎቹ በ1861 እ.ኃ.ዘ.አ. ከአቡኑ እጅ በመጥፋታቸው (ሙሉ) ዝርዝራቸው ማወቅ አልተቻለም፤ የሚቻልም አይመስልም። ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ በአቡኑ ሐሳብና ዕውቅና ካከናወናቸው የትርጉም ስራዎች የተገኘው በቫቲካን ቤተ-መጻሕፍት የሚገኘው እና 165 እንደ መለያ ቁጥር የተሰጠው ሰነድ ብቻ ነው። ይኽ ጽሑፍ የፍራንሷ በርጌድ 'የቅርጣግና ሌሊቶች' የተሰኘ መጽሐፍ ግእዝ ትርጉም ነው። የዚኽ መጽሐፍ አማርኛ ትርጉም በኢትዮጵያ የብራና ጽሑፎች ማይክሮ ፊልም ቤተ-መጻሕፍት ቁጥር 1470 ተመዝግቦ ይገኛል። በውስጡ ያለው ጽሑፍም ከጁስቶ ዳ ኡርቢኖ (አባ ዮስጦስ) ግእዝ ትርጉም ወደ አማርኛ እንደተገለበጠ ያስረዳል።

ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ 7 ሰኔ 1855 እ.ኃ.ዘ.አ. ወደ አንታን ዲ አባዲ በጻፈው ደብዳቤ ከኢትዮጵያ በተባረረበት ወቅት በነበረ ግርግር ቢያንስ ሶስት መጻሕፍት እና ዘጠኝ ማስታወሻዎች እንዳጣ ይገልጻል (Wion 2012) ።

ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ በ1855 እ.ኃ.ዘ.አ. ከኢትዮጵያ ተባርሮ ከወጣ በኋላ በግብጽ ካይሮ ቆይታውም Vicende politiche e religiose in Abissinia dopo il 1852 በሚል ርዕስ በSpettatore egiziano የተሰኘ የጣልያንኛ መጽሔት ሶስት ተከታታይ መጣጥፎች አሳትመዋል[72] (Sumner 1976)።

ጁስቶ ኡርቢኖ በ1856 እ.ኃ.ዘ.አ. በሱዳን ሲሞት ደግሞ በእጁ የነበሩ መጻሕፍት እና ማስታወሻዎች በኢጣሊያ ሮማ ለነበሩ የበላይ ሐላፊዎቹ ተልከዋል። እነዚኽ ሰነዶች በቫቲካን ቤተ-መጻሕፍት ይገኛሉ[73] (Wion 2013) ።

በተጨማሪ Propositio Liguae Aethiopicae scripta in Aethiopia 1850-54 የሚል ርዕስ ያለው እና የእጅ ጽሑፍ 167[74] በሚል መለያ የሚታወቀው መዝገበ ቃላት በሮም ቤተ-መጻሕፍት[75] እንዲኹም በሌላ የሮም ቤተ-መጻሕፍት[76] የሚገኘው በመለያ ቁጥር ምስራቃዊ 134[77] የሚታወቀው የሰዋስው መጽሐፍ የጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የስራ ውጤቶች ናቸው።

ከላይ እንደተገለጸው ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ከሰበሰባቸው ወይም ካሰባሰባቸው እና ከተረጎማቸው በርካታ መጻሕፍት መካከል የዳዊት መዝሙር ፈጽሞ አይገኝም። በጠፉ(በ)ት እና ባቃጠላቸው ስራዎቹም የዳዊት መዝሙር መኖሩ የሚያመላክቱ ፍንጮች ጭራሽኑ የሉም። የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ ግን ለየዳዊት መዝሙር የተለየ ፍቅር እና አክብሮት ያደረበት እንደነበረ ፈጽሞ መካድ አይቻልም። ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ ቢኾን ኑሮ በግልጽ የሚታወቀው የዳዊት መዝሙር ፍቅሩ ባሰባሰባቸው (ሌሎች) መጻሕፍት ለየዳዊት መዝሙር ያለው ክብር ደግሞ በጻፋቸው (ሌሎች) ጽሑፎች ማንፀባረቁ አይቀርም ነበር።

5.1. *የጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ጽሑፎች እና መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ*

ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ራሱ የጻፋቸውና የተረጎማቸው መጻሕፍት አምስት ናቸው። እነሱም ዲ አባዲ 216 ሰዋስው፣ ዲ አባዲ 217 መዝገበ ቃላት፣ የእጅ ጽሑፍ 167 መዝገበ ቃላት፣ ምስራቃዊ 134 ሰዋስው እንዲኹም ቫቲካን 165 የትርጉም ስራ ናቸው። ከእነዚኽ መጻሕፍት በአንድም በሌላም መንገድ የዳዊት መዝሙር ከሚጠቅሱ ዲ አባዲ 216 አንዱ ነው።

የዳዊት መዝሙር ከየግዕዝ ቅኔ ዓይነቶች ገለጻ ጋር ተያይዞ በ ዲ አባዲ 216[78] ቢያንስ አምስት ጊዜ ተጠቅሷል። እነዚኽም ገጽ 120 የቀኝ ቅጠል የዳዊት መዝሙር 62 "ዘአምላኪየ"፣ ገጽ 121 የግራ ቅጠል የዳዊት መዝሙር ምዕራፍ 3 "ሚበዝሁ"፣ ገጽ 134 የቀኝ ቅጠል የዳዊት መዝሙር ምዕራፍ 86 ቁጥር 3 "ነኪር ነገሩ በእንቲአኪ ሀገረ እግዚአብሔር"፣ ገጽ 141 የቀኝ ቅጠል የዳዊት መዝሙር ምዕራፍ 92 ቁጥር 1 "እግዚአብሔር ነግሰ"፣ ገጽ 121 የግራ ቅጠል የዳዊት መዝሙር 149 "ክብርት ይእቲ" ናቸው (Ethiop_Abb_216) ።

እነዚኽ በ ዲ አባዲ 216 የተጠቀሱት የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ከሚገኙ ጥቅሶች ጋር (ብዙ) የይዘት ወይም መልዕክት ግንኙነት የላቸውም። ይኽም ጆስቶ ዳ ኡርቢኖ በስራዎቹ ለየዳዊት መዝሙር የሰጠው ትኩረት ጥልቅ እንዳልኾነ ያመለክታል። ለየዳዊት መዝሙር ጥቅሶች ትኩረት አለመስጠት ደግሞ በየዳዊት መዝሙር ያጌጠ መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ የጻፈ ጸሐፊ (መለያ) ባህርይ አይደለም፤ ሊኾንም አይችልም።

5.2. *ጆስቶ ዳ ኡርቢኖ እና መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ (ዲ አባዲ 234)*

ጆስቶ ዳ ኡርቢኖ በእጁ ገልብጦ በጻፈው ዲ አባዲ 234 ቅጂ ከቅዱሳት መጻሕፍት የተወሰዱ ብዙ ጥቅሶች ምልክት አድርጎባቸዋል። ይኹን እንጂ ከየዳዊት መዝሙር ተወስደው ምልክት ሳያደርግባቸው የቀሩ ጥቅሶችና አገላለጾችም አሉ።

ጆስቶ ዳ ኡርቢኖ ምልክት ሳያደረግባቸው ከቀሩት ጥቅሶች በምዕራፍ 7 የሚገኝ "ዘይፈድዮ ለኵሉ በከመ ምግባሩ" የሚል የዳዊት መዝሙር 61፥12 ንባብ እና በምዕራፍ 9 የሚገኝ "ወመጽአኒ ድንጋፄ ሞት" የሚል የዳዊት መዝሙር 54፥4 ንባብ ዋነኞቹ ናቸው። የሚገርመው ደግሞ ጆስቶ ዳ ኡርቢኖ ራሱ በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ዲ አባዲ 215 መጨረሻ በጨመረው "እስመ አረጋዊ አነ ጥቀ ወርዘውኩሂ ወረሳዕኩ። ጻድቀሰ ዘይትገደፍ ኢርኢኩ። ወዘርዐሂ ኢይፄነስ እክለ። ወውስተ በረከት ይሄሉ ለዓለመ ዓለም" የሚል የዳዊት መዝሙር 36፥25-26 ንባብም ምልክት ሳያደርግበት ቀርቷል።

በተጨማሪም በምዕራፍ 10 የሚገኝ "አንሰ ነዳይ ወምስኪን አነ" የሚል የዳዊት መዝሙር 39፥17 ንባብ እና በምዕራፍ 10 የሚገኘ "ስብሐተ ሐዲሰ" የሚል የዳዊት መዝሙር 95፥1 ንባብም ምልክት ያላደረገባቸው ጥቅሶች ናቸው። የዳዊት መዝሙር 50፥8 ንባብ ዳግመኛ ሲጠቀስም ምልክት ሊደረግለት በሚገባ ቦታ ሳይጻፍለት ቀርቷል። ምልክት ሳያደርግባቸው የቀሩ ብዙ የዳዊት መዝሙር አገላለጾችም አሉ። (ንጉሥ 2016)

በመኾኑም ይኽ መረጃ ኹለት ነገር ያመለክታል። አንድ ከላይ ተዘርዝሮ እንደተገለጸው በእርግጥ ጆስቶ ዳ ኡርቢኖ ምልክት ሳያደረግባቸው የቀሩ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-

ያዕቆብ ዲ አባዲ 234 ጥቅሶች በቁጥር ጥቂት ናቸው። ቢኾንም ምልክት ሳይደረግባቸው የቀሩ ጥቅሶችና አገላለጾች የጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የዳዊት መዝሙር ዕውቀት ወይም ትኩረት በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ እንዳለው የተሟላ እንዳልኾነ በደንብ ያሳያሉ።

በሌላ መልኩ ደግሞ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች ቁጥሮች ራሱ በእጁ ገልብጦ በጻፈው ቅጂ ዲ አባዲ 234 (ብቻ) በጎዳግ ለምን መጨመር እንደቻለ መጠየቅ ያስፈልጋል። ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ ቢኾን ኑሮ ሲጀመር የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች ቁጥሮች በጎዳግ መጨመር አያስፈልገውም ነበር።

ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ በአጁ ገልብጦ በጻፈውና ወደ አንቷን ዲ አባዲ በፖስታ በላከው ዲ አባዲ 234 መጽሐፍ ውስጥ ራሱ ኡርቢኖ በ28 የካቲት 1853 ያሰፈረው የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች ቁጥሮች በጎዳግ ለምን መጨመር እንደቻለ የሚያመላክት ማስታወሻ አለ። በማስታወሻውም "የዘርዐ-ያዕቆብ መጽሐፍ በተመለከተ ያገኘሁት በአጋጣሚ ነው፤ አላስተዋልኩትም ነበር። ነገር ግን ከወታደር ልጆች አንዱ ከደምቢያ ዘመቻ በመመለስ ሳለ የዳዊት መዝሙር መግዛት እፈልግ እንደኾነ ጠየቀኝ (እኚኽ ልጁ የተጠቀማቸው ቃላት ናቸው)፤ እኔም መጽሐፉን አይቼ ምን እንደኾነ ካወቅኩ በኋላ ገዛሁት።" ይላል።

በዚኽ ደብዳቤ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ እንደየዳዊት መዝሙር ይቆጠር እንደነበረ ይነግረናል፤ በቂ ፍንጭም ይሰጠናል። እሱ ግን አይቶ መጽሐፉ የዳዊት መዝሙር ሳይኾን ቀድሞ አይቶት የነበረ መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ወይም ያዕቆብ መኾኑን ለይቶ እንዳወቀው ያስረዳናል። በመኾኑም በየዳዊት መዝሙር ያሸበረቀ መጽሐፍ እንደሃገሩ ልማድ እንደየዳዊት መጽሐፍ አለመቁጠሩና ይኽ ለማረጋገጥም በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ያሉ የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች ለይቶ በጎዳግ ለማሳየት መሞከሩ እንገነዘባለን።

ይኹን እንጂ ከላይ እንደተገለጸው መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ በየዳዊት መዝሙር ጥቅሶች የተዋበ ጽሑፍ ብቻ ሳይኾን የዳዊት መዝሙር እንደ የሕይወት መርህ ተተግብሮ በጥልቀት የተተነተነበት ግለ ታሪክ እና ዓውድ ነው። ይኽ ማስረጃ በበኩሉ ደግሞ ዛሬ አንዳንዴ እንደሚነሳው መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ በሌሎች እርዳታ የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች እዚም እዛም ሰክቶና ከትቶ ሊጽፈው የሞከረ ድርሰት ሊኾን እንደማይችል ያጸናል። በሌላ በኩል ደግሞ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ከየዳዊት መዝሙር የተለየ ጽሑፍ መኾኑን ለማስረዳት የኼደበት ርቀት የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ እንዳልኾነና የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ ያኽል የዳዊት መዝሙር ዕውቀት እንዳልነበረው በግልጽ ያሳያል።

5.3. ጆስቶ ዳ ኡርቢኖ እና የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ቅጂዎች

አብዛኛዎቹ በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ዲ አባዲ 215 ይኹን ዲ አባዲ 234 የሚገኙ የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች በግልጽ ቃል በቃል የተጠቀሱ ናቸው። ቢኾንም በኹለቱ የሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ቅጂዎች ከሚገኙ እነዚኽ የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች የቃል አጻጻፍ ልዩነት የሚታይባቸው (የተወሰኑ) ንባቦች አሉ። በጣም ጥቂት የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች ደግሞ በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ዲ አባዲ 215 ተከልሰው ቢቀርቡም በ ዲ አባዲ 234 ግን ቃል በቃል ቀርቧል (ንጉሥ 2016) ።

የተቀሩት በ ዲ አባዲ 215 እንዲኹም በ ዲ አባዲ 234 የሚገኙ የዳዊት መዝሙር ጥቂት ጥቅሶች ደግሞ በጽሑፉ የገቡበት ኹኔታ እንዲስማሙ ተለውጠው ወይም ተስተካክለው የቀረቡ ናቸው። ከእነዚኽ አብዛኛዎቹ የባለቤት መደብ በመቀየር የተፈጠሩ ለውጦች ወይም ማስተካከያዎች ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ የሐሳብ ክለሳ የተደረገባቸው ናቸው።

በኹለቱም የሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ቅጂዎች ባሉ ጥቂት የተከለሱ የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች በተለያዩ ምክንያቶች የተፈጠሩ የአጻጻፍ ልዩነቶች አሉ። ለዚኽ ዋነኛ ማሳያ ደግሞ በምዕራፍ 11 የሚገኝ "እፈቅድ እንበር በሰላም ወበፍቅር ምስለ ኵሉ ሰብእ ወአበድር ፍሬ ፃማየ እሴሰይ። ወእትገደፍ በጎበ ሰብእ ወእንበር ጎቡእ በጥበብ እንተ አለበወኒ እግዚአብሔር እምእንበር ክቡረ ውስተ ቤተ ኃጥአን" የሚል የዳዊት መዝሙር 83፥10 ንባብ ነው።

ይኽ ንባብ ከሌሎች ንባቦች በተለየ መልኩ የተከለሰ መኾኑ ተረድቶ ጆስቶ ዳ ኡርቢኖ በ ዲ አባዲ 234 ከየዳዊት መዝሙር 83 የተወሰደ እንደኾነ ገልጸዋል። በመኾኑም ንባቡ ቢያንስ ኹለት ነገር ያመለክታል። አንድ በምዕራፍ 4 "ገሥጸኒ አንተ በጽድቅ ወተዛለፈኒ በምሕረት። ወቅብዓ ኃጥአንሰ ወሐሳውያን መምህራን ኢይትቀባዕ ርእስየ"፥ በምዕራፍ 7 "ፈጣሪሰ ይስሕቆመ ወእግዚአ ፍጥረት ይሣለቅ ላዕሌሆመ" እንዲኹም በምዕራፍ 7 "ወኵሉ ፍኖቱ ጽድቅ ወርትዕ" የሚሉ እና በ ዲ አባዲ 215 የሚገኙ ተመሳሳይ የተከለሱ ንባቦች በመሰረቱ ያልተሳሳቱ እና በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ አጻጻፍ የተለመዱ እንደኾኑ ያሳያል። በሌላ መንገድ ደግሞ የተከለሱበት መንገድ የተለየ እንዳልኾነ ይገልጻል።

ኹሉም የተከለሱበት መንገድ በምዕራፍ ድርሰት እና የዳዊት መዝሙር ከሚገኝ ዘይኤ የሚመሳሰል ነው። ጆስቶ ዳ ኡርቢኖ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ ቢኾን ኖሮ ግን የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች ቁጥሮች በጎዳግ ከመጨመር አልፎ የዳዊት መዝሙር 83፥10 ምንባብ ላይ ከሌሎች የዳዊት መዝሙር ምንባቦች ጭምር የተለየ መኾኑ ለማሳየት ምልክት የሚያደርግበት አንዳች ምክንያት የለውም፤ አይኖረውም።

5.4. ጆስቶ ዳ ኡርቢኖ የዳዊት መዝሙር እና የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ቅጂዎች

አብዛኛዎቹ በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ዲ አባዲ 215 የሚገኙ የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች በ ዲ አባዲ 234 በግልጽ ቃል በቃል ተጠቅሰው የሚገኙ ናቸው። በመሆኑም የዳዊት መዝሙር በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ኹለቱም ቅጂዎች የተዘራበት ወይ የተገለጸበት መንገድ ጉልህ ተመሳሳይነት እና ወጥነት ያለው ነው። ይኽ እንዳለ ኾኖ ግን በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ቅጂዎች ያሉ ጥቅሶች የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ልዩነት፣ የፊደላት አጻጻፍ ልዩነት፣ በስሕተት ወይም ግድፈት የተነሳ የተፈጠረ የቃላት አጻጻፍ ልዩነት እንዲኹም ከዋናው የዳዊት መዝሙር አንጻር የንባብ ልዩነት ይታይባቸዋል። እነዚኽ ኹሉ ልዩነቶች ደግሞ ስምምነት የላቸውም፤ ወጥነትም ይጎድላቸዋል።

ለምሳሌ በክፍል አንድ የሚገኝ ኹለተኛው የዳዊት መዝሙር ንባብ ምዕራፍ 33 ቁጥር 2 እስከ 5 የሚጠቅስ ነው። ንባቡም በቅጂዎቹ እንዲኽ ተደርጎ ተጽፏል።

- ወበእግዚአብሔር ትክበር ነፍስየ ይስምዑ የዋሃን ወይትፈሥሑ። እስመ አነ ኃሠሥክዎ ለእግዚአብሔር ወተሰጥወኒ ወይእዜኒ አንትሙኒ ቅረቡ ኀቤሁ ወያበርህ ለክሙ። ወኢይትኀፈር ገጽክሙ። አዕብይዎ ለእግዚአብሔር ምስሌየ። ወናልዕል ስሞ ኀቡረ (ዲ አባዲ 215)
- ወበእግዚአብሔር ትከብር ነፍስየ ። ይስምዑ የዋሃን ወይትፈሥሑ እስመ አነ ሐሠሥክዎ ለእግዚአብሔር ወተሠጥወኒ። ወይእዜ አንትሙኒ ቅረቡ ኀቤሁ ወያበርህ ለክሙ ወኢይተኀፈር ገጽክሙ አዕብይዎ ለእግዚአብሔር ምስሌየ ወናልዕል ስሞ ኀቡረ። (ዲ አባዲ 234)

የቅጂዎቹ ንባቦች የአምስት ቃላት የአጻጻፍ ልዩነት ይታይባቸዋል። አንደኛው ቃል በ ዲ አባዲ 215 'ትክበር' ሲል በ ዲ አባዲ 234 'ትከብር' ይላል። ኹለተኛው ቃል በ ዲ አባዲ 215 'ኃሠሥክዎ' ሲል በ ዲ አባዲ 234 'ሐሠሥክዎ' ይላል። ሶስተኛው ቃል በ ዲ አባዲ 215 'ወተሰጥወኒ' ሲል በ ዲ አባዲ 234 'ወተሠጥወኒ' ይላል። አራተኛው ቃል በ ዲ አባዲ 215 'ወይእዜኒ' ሲል በ ዲ አባዲ 234 'ወይእዜ' ይላል። አምስተኛው ቃል በ ዲ አባዲ 215 'ወኢይትኀፈር' ሲል በ ዲ አባዲ 234 'ወኢይተኀፈር' ይላል። ልዩነቱ በሥርዐት ሲታይ በ ዲ አባዲ 215 ያለውን የአምስቱ ቃላት አጻጻፍ የተሻለ ነው።

ንባቡ "በእግዚአብሔር ትክበር ነፍስየ ይስምዑ የዋሃን ወይትፈሥሑ። ኃሠሥክዎ ለእግዚአብሔር ወተሰጥወኒ፤ ቅረቡ ኀቤሁ ወያበርህ ለክሙ ወኢይትኀፈር ገጽክሙ። አዕብይዎ ለእግዚአብሔር ምስሌየ፤ ወናልዕል ስሞ ኀቡረ።" ከሚለው ዋናው የዳዊት መዝሙር ሐሳብ ጋር ሲነጻጸር ደግሞ በተወሰነ መልኩ እንደተለወጠ እንረዳለን።

በተጨማሪ የቅጂዎቹ ንባቦች በየራሳቸው ኾነ ከዋናው ሐሳብ ጋር ሲነጻጸሩ ሰፊ የሥርዐተ ነጥብ ልዩነት ይታይባቸዋል። ከኹለቱ ቅጂዎች በንጽጽር በ ዲ አባዲ 215 ያለውን (የሥርዐተ ነጥብ አቀማመጥ ወይ አጠቃቀም) ቢሻልም ኢኖ ሊትማን ግን አብልጦ በዚኽ መልኩ አርሞታል፦

- ወበእግዚአብሔር ትክበር ነፍስየ ይስምዑ የዋሃን ወይትፈሥሑ። እስመ አነ ኃሠሥክዎ ለእግዚአብሔር ወተሰጥወኒ፤ ወይእዜኒ አንትሙኒ ቅረቡ ኀቤሁ ወያበርህ ለክሙ ወኢይትኀፈር ገጽክሙ። አዕብይዎ ለእግዚአብሔር ምስሌየ፤ ወናልዕል ስሞ ኀቡረ።

በተጨማሪ ‘ኃሠሥክዎ’ የሚል ቃል በ ዲ አባዲ 215 ወጥነት ባለው መልኩ ቢጻፍም በ ዲ አባዲ 234 ግን በተደበላለቀ መልኩ ተጽፈዋል። ‘ወተሰጥወኒ’ የሚል ቃል ደግሞ በ ዲ አባዲ 234 ኾነ በ ዲ አባዲ 215 ወጥ አጻጻፍ አለው፤ ግን በፊደላት አጠቃቀም ይለያያል። ‘ወኢይትኀፈር’ የሚል ቃል በ ዲ አባዲ 215 የአጻጻፍ ወጥነት ይጎድለዋል በ ዲ አባዲ 234 ግን የአጻጻፍ ወጥነት አለው።

ሌላው ምሳሌ በክፍል አራት የሚገኝ ኹለተኛው የዳዊት መዝሙር ንባብ ኾኖ ከምዕራፍ 118 ቁጥር 70 የተጠቀሰ ነው።

- ረግዓ ከመ ሐሊብ ልቦሙ (ዲ አባዲ 215)
- ረግዓ ከመ ሐሊብ ልቦሙ (ዲ አባዲ 234)

በኹለቱ ቅጂዎች ንባብ የአጻጻፍ ወይም የአገባብ ልዩነት የለም። ቢኾንም ‘ረግዓ’ የሚል ቃል ተስተካክሎ ‘ረግዐ’ ተብሎ መጻፍ ነበረበት። ‘ረግዐ’ የሚል ቃል በኹለቱም ቅጂዎች ሲጻፍ በተመሳሳይ መልክ ቀርቧል። ቃሉ በኹለቱም ቅጂዎች የተጻፈበት መንገድም ወጥነት የለውም።

ተጨማሪ ምሳሌ በክፍል ሰባት ያለ ሶስተኛው ንባብ እና ከምዕራፍ 9 ቁጥር 16 የተወሰደ የዳዊት መዝሙር ጥቅስ ነው። ጥቅሱ ከዋናው የዳዊት መዝሙር ንባብ አንጻር ቀጥሎ እንደተመለከተው የሐሳብ መከለስ ይታይበታል።

- እለ ይነስቱ ሥርዓተ ፈጣሪ ይሠገሩ በግብረ እደዊሁ። (ዲ አባዲ 215)
- እለ ይነሥቱ ሥርዓተ ፈጣሪ ይሠገሩ በግብረ እደዊሁ (ዲ አባዲ 234)

በኹለቱም ቅጂዎች ንባቡ ላይ የአንድ ቃል አጻጻፍ ወይም አገባብ ልዩነት አለ። በንጽጽር ‘ይነሥቱ’ የሚለው ቃል በ ዲ አባዲ 234 በሚገባ ሥርዐት ተጽፈዋል። ኾኖም

‘ይነሥቱ’ የሚል ቃል በኹለቱም ቅጂዎች የተጻፈበት መንገድ ተመሳሳይ አይደለም። በዛ ላይ ደግሞ ወጥነትም ይጎድለዋል።

ሌላ ምሳሌ ቀጥሎ የቀረበው ንባብ እና በክፍል ዘጠኝ ያለ ስድስተኛው የዳዊት መዝሙር ጥቅስ ሲኾን በምዕራፍ 118 ቁጥር 134 ይገኛል።

- አድኅነኒ እምትዕግልተ እንለ እመሕያው (ዲ አባዲ 215)
- አድኅነኒ እምትዕግልተ ዕንለ እመሕያው። (ዲ አባዲ 234)

ንባቡ በተመለከተ በቅጂዎቹ የአንድ ቃል አጻጻፍ ልዩነት ይታይባቸዋል። ቃሉ በ ዲ አባዲ 215 ‘እንለ’ ተብሎ ሲጻፍ በ ዲ አባዲ 234 ደግሞ ‘ዕንለ’ ተብሎ ተጽፏል። ትክክለኛው የቃሉ አጻጻፍ በ ዲ አባዲ 234 ያለውን ነው። በተጨማሪ የንባቡ ሥርዐተ ነጥብ አቀማመጥ ሲታይ በ ዲ አባዲ 234 ያለውን መንገድ ይሻላል።

‘ዕንለ’ የሚለው ቃል በ ዲ አባዲ 215 የተጻፈበት መንገድ ስሕተት ቢኾንም ወጥነት ግን አለው። በ ዲ አባዲ 234 ደግሞ አንዳንዱ በትክክለኛው አንዳንዱ በተሳሳተ አካኋን ተጽፈዋል።

ሌላ ተጨማሪ ምሳሌ በክፍል አስራ ኹለት ያለ የመጨረሻው የዳዊት መዝሙር ጥቅስ ሲኾን በምዕራፍ 108 ቁጥር 1 የሚገኘውን ቀጣይ ንባብ ነው።

- ወዘየወኟ እግዚኦ ኢትጸመመኒ (ዲ አባዲ 215)
- ወበመዝሙር ዘየኟ እግዚኦ ኢትጸመመኒ (ዲ አባዲ 234)

ቅጂዎቹ ሲጠቅሱ አንድ የቁጥር አጻጻፍ እና አንድ የቃል አጻጻፍ ልዩነት ይታይባቸዋል። ቁጥሩ በ ዲ አባዲ 215 ‘ዘየወኟ’ ተብሎ ሲጻፍ በ ዲ አባዲ 234 ደግሞ ‘ዘየኟ’ ተብሎ ተጽፈዋል። ትክክለኛው የቃሉ አጻጻፍ በ ዲ አባዲ 215 ያለውን ነው። በተጨማሪ በ ዲ አባዲ 215 ‘ወዘየወኟ’ ተብሎ ሲጻፍ በ ዲ አባዲ 234 ‘ወበመዝሙር ዘየኟ’ ተብሎ ተጽፈዋል። ኹለቱም አጻጻፎች በደንብ ያስኬዳሉ ግን በ ዲ አባዲ 215 ያለውን አጻጻፍ ይመረጣል።

የቁጥሮች አጻጻፍ በኹለቱም ቅጂዎች ዘንድ ወጥነት የለውም። በንጽጽር ሲታይ ግን በ ዲ አባዲ 215 ያለውን ወጥነት ይሻላል።

ሌላ ምሳሌ ቀጥሎ እንደቀረበው በመጨረሻው ክፍል ያለው ኹለተኛው እና ከየዳዊት መዝሙር ምዕራፍ 36 ቁጥር 25 እና 26 የተወሰደ ጥቅስ ነው።

- እስመ አረጋዊ አነ ጥቀ ወርዘውኩሂ ወረሣእኩ። ጻድቀሰ ዘይትገደፍ ኢርኢኩ። ወዘርኡሂ ኢይዜነስ እክለ። ወውስተ በረከት ይሄሉ ለዓለመ ዓለም (ዲ አባዲ 215)
- እስመ አረጋዊ አነ ጥቀ ወወርዘውኩሂ ወረሳዕኩ ጻድቀሰ ዘይትገድፍ ኢርኢኩ ወዘርኡሂ ኢይጼንስ እክለ ወውስተ በረትት ይሄሉ ለዓለመ ዓለም። (ዲ አባዲ 234)

በዋናው የዳዊት መዝሙር ያለው ንባብ “ወርዘውኩሂ ወረሳእኩ፤ ወጻድቅሰ ዘይትገደፍ ኢርኢኩ፤ ወዘርዐኒ ኢይጼነስ እክለ። ወዘርዐሂ ውስተ በረከት ይሄሉ።” ይላል። በቅጂዎቹ የቀረበው ጥቅስ ግን በመጠኑም ቢኾን የተለወጠ ነው።

ቅጂዎቹ የስድስት ቃላት የአጻጻፍ ልዩነት ይታይባቸዋል። አንደኛው ቃል በ ዲ አባዲ 215 ‘ወርዘውኩሂ’ ሲል በ ዲ አባዲ 234 ‘ወወርዘውኩሂ’ ይላል። በ ዲ አባዲ 215 ያለውን ይሻላል። ኹለተኛው ቃል በ ዲ አባዲ 215 ‘ወረሣእኩ’ ሲል በ ዲ አባዲ 234 ‘ወረሳዕኩ’ ይላል። በ ዲ አባዲ 234 ያለውን ይሻላል። ሶስተኛው ቃል በ ዲ አባዲ 215 ‘ዘይትገደፍ’ ሲል በ ዲ አባዲ 234 ‘ዘይትገድፍ’ ይላል። በ ዲ አባዲ 215 ያለውን ይሻላል። አራተኛው ቃል በ ዲ አባዲ 215 ‘ወዘርኡሂ’ ሲል በ ዲ አባዲ 234 ‘ወዘርኡሂ’ ይላል። ትክክለኛው የቃሉ አጻጻፍ ‘ወዘርዐሂ’ ነው። ስለኾነ በኹለቱ ቅጂዎች ያሉ አጻጻፎች የተሳሳቱ ናቸው። አምስተኛው ቃል በ ዲ አባዲ 215 ‘ኢይዜነስ’ ሲል በ ዲ አባዲ 234 ‘ኢይጼንስ’ ይላል። ትክክለኛው የቃሉ አጻጻፍ ‘ኢይጼነስ’ ነው። ስድስተኛው ቃል በ ዲ አባዲ 215 ‘በረከት’ ሲል በ ዲ አባዲ 234 ‘በረትት’ ይላል። በ ዲ አባዲ 215 ያለውን ይሻላል። በ234 ያለው ደግሞ በስሕተት የተጻፈና ሳይታረም የቀረ ነው። ከዚኽ በተቃራኒ ግን በ ዲ አባዲ 234 ‘ወጥቀ’ ተብሎ ተጽፎ የነበረውን ታርሞ ‘ጥቀ’ ኾነዋል። ‘ዘትገድፍ’ ተብሎ ተጽፎ የነበረውን ደግሞ ታርሞ ‘ዘይትገድፍ’ ተደርጎ ተስተካክለዋል። ከዚኽ ውጪ በንጽጽር የንባቡ ሥርዐተ ነጥብ አቀማመጥ በ ዲ አባዲ 215 ያለውን ይሻላል።

‘ዘርዐ’ የሚል ቃል በ ዲ አባዲ 234 በተሻለ የአጻጻፍ ወጥነት ቀርቧል። ቃሉ በ ዲ አባዲ 215 የቀረበበት አጻጻፍ ግን የተደበላለቀ ነው። አንዳንዴ በትክክለኛው አንዳንዴ በተሳሳተ አካኋን ተጽፈዋል።

እነዚኽ ኹሉ ምሳሌዎች በ ዲ አባዲ 234 እና ዲ አባዲ 215 ጸሐፊዎች እና ምንጮች ልዩነቶች እንዳሉ ያመላክታሉ። ኾኖም ኹለቱ ቅጂዎች አንዱ ከአንዱ የሚለይበት ወጥ የኾነ ወይም የተሻሻለ የአጻጻፍ አካኋን ወይም የጥቅስ አወሳሰድ ዓውድ እንዲኹም የሥርዐተ ነጥብ አጠቃቀም አገባብ አይታይባቸውም።

ኹለቱም የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ቅጂዎች በተለያዩ ሰዎች ተጽፈዋል። ኾኖም ከጽሑፎቹ (ዲ አባዲ 234፣ ዲ አባዲ 216 ጨምሮ እና ሌሎች) እንደምንረዳው ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ስራዎቹ ተመልሶ የማረም ልምድ ነበረው። ኹለቱም የሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ቅጂዎችም በራሱ በጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ታርመዋል። ዲ አባዲ 234 ራሱ ያቀዳውና ራሱ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ በተመሳሳይ እጅና ብዕር እንዳረመው የሚያሻማ አይደለም። ዲ አባዲ 215 የቀዳው ግን ኢትዮጵያዊ ጸሐፊ ይመስላል። ይኽ ጸሐፊ መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ በተመሳሳይ እጅና ብዕር ያረመበት መንገድ ደግሞ ኢትዮጵያውነቱ በሚገባ ያጸናል (Mbodj and Wion 2013; Wion 2013a; Wion 2013b)።

ዲ አባዲ 215 በሌላ እጅና ብዕርም አርትዖት ተሰርቶበታል። በ ዲ አባዲ 215 ውስጥ በ ዲ አባዲ 234 ያለውን የጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የእጅ ጽሑፍም ቁልጭ ብሎ ይታያል። ለምሳሌም በ ዲ አባዲ 215 መጨረሻ የጎደለውን ለማሟላት የተጨመረ ንባብ በጁስቶ ዳ ኡርቢኖ እንደተጻፈ እጅግ ግልጽ ነው (Ethiop_Abb_234; Ethiop_Abb_215)።

ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ዲ አባዲ 215 መጽሐፍ የቻለውን ያክል ቢያርመውም በመጽሐፉ የሚገኙ ጥቅሶች የተወሰዱበት መጽሐፍ የሚያሳዩ ምልክቶች ግን አላደረገበትም። ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ ቢኾን ኖሮ ምልክቶቹ በኹሉም ቅጂዎች ወጥነት ባለው መልኩ ይተገበሩ ወይ ሳይተገበሩ ይቀሩ ነበር።

በተጨማሪ እጅግ በጣም ጥቂት ቢኾኑም በ ዲ አባዲ 234 የሚገኙ በ ዲ አባዲ 215 ግን የሌሉ እንዲኹም በ ዲ አባዲ 215 ያሉ በ ዲ አባዲ 234 ግን የማይገኙ የዳዊት መዝሙር ጥቅሶች ወይም ንባቦች አሉ። ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ ቢኾን ኖሮ ራሱ ባረማቸው ኹለት ቅጂዎች እንዲኽ ዓይነት መፋለስ ሲፈጸም ሳያስተካክል የሚያልፍበት ዕድል ጠባብ ነው።

በኹለቱ ቅጂዎች የሚገኙ ተመሳሳይ የዳዊት መዝሙር ጥቅሶችም ቢኾኑ የአጻጻፍና አቀራረብ ወጥነት ወይም መሻሻል አይታይባቸውም። የ ዲ አባዲ 215 ቅጂ ከ ዲ አባዲ 234 ቅጂ በኋላ የተጻፈ በመኾኑ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ ቢኾን ኖሮ በ ዲ አባዲ 234 የተከተላቸው የአጻጻፍና አቀራረብ ቅዶች በ ዲ አባዲ 215 ሊቀጥልባቸው ወይም ሊያሻሽላቸው ይጠበቃል። ይኹን እንጂ ከ ዲ አባዲ 234 አንጻር በ ዲአባዲ 215 ያለ የአጻጻፍና አቀራረብ ቅድ በብዙ መንገድ ይለያል፤ በአንዳንድ መስፈርትም ያንሳል። ኹለቱም ቅጂዎች ያረመ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ አንዱ ከሌላኛው የሚያስበልጥ ተገቢ ማስተካከያ ሳያደርግባቸው አልፈዋል። ይኽም ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የዓይነተኛው መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ አድርጎ መውሰድን (እጅግ) አዳጋች ያደርገዋል።

5.5. የጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ሰራዎች እና የስራ ሥነ-ምግባር

ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ወደ እህቱ፣ ጓደኛው፣ የበላይ ሐላፊዎቹ፣ አንቷን ዲ አባዲ እና ጥቂት ሌሎች ሰዎች በርካታ ደብዳቤዎች ጽፏል። የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ኹለቱም ቅጂዎች ጨምሮ በኢትዮጵያ ቆይታው የሰበሰባቸው 20+ መጻሕፍት ለአንቷን ዲ አባዲ ልኮለታል። ቢያንስ አምስት መጻሕፍት ሊጽፍና ሊተረጉምም ችለዋል። ከኢትዮጵያ በተባረረበት ወቅት በነበረ ግርግርም ቢያንስ 3 መጻሕፍት እና 9 ማስታወሻዎች አጥቷል። በ1855 እ.ኃ.ዘ.አ. ከኢትዮጵያ ተባርሮ ከወጣ በኋላ ደግሞ በግብጽ ካይሮ ቆይታውም Vicende politiche e religiose in Abissinia dopo il 1852 በሚል ርዕስ በSpettatore egiziano የተሰኘ የጣልያንኛ መጽሔት 3 ተከታታይ መጣጥፎች አሳትሟል። በ1856 እ.ኃ.ዘ.አ. በሱዳን ሲሞት ደግሞ በእጁ የነበሩ መጻሕፍት እና ማስታወሻዎች በኢጣሊያ ሮማ ለነበሩ የበላይ ሐላፊዎቹ ተልከዋል። እነዚኽ ሰነዶችም በቫቲካን ቤተ-መጻሕፍት ይገኛሉ። በጥቂት ዓመታት ይኽ ኹሉ ስራ ያበረከተው ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ላይ ከመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ማሰባሰብ ስራው ውጪ የማስመሰል ክስ ሲቀርብበት አይታይም። ይልቅኑ የአንቷን ዲ አባዲ የመጻሕፍት ዝርዝር መዝገብ በአዳዲስ መጻሕፍት ለመሙላት ያደረገው ጥረትና 20+ መጻሕፍት ለአንቷን ዲ አባዲ በመላክ ያሳካው ውጤትና ያበረከተው አስተዋጽኦ እጅግ የሚደነቅ ነው። በመኾኑም ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ከሚታወቅበት የስራ ሥነ-ምግባር አንጻር እሱን መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ በማስመሰል እንደጻፈ ለመክሰስ የሚያበቃ በቂ ምክንያት ወይ አሳማኝ ማስረጃ የለም።

5.6. ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ እና የጠፉት መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ቅጂዎች

የጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ገለጣ እውነት ከኾነ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ከ ዲ አባዲ 234 እና ከ ዲ አባዲ 215 ውጪ ቢያንስ ሶስት የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕብ ቅጂዎች እና አንድ የትርጉም ስራ ነበሩ።

የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ የመጀመሪያው ቅጂ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ በጥሩ ኹኔታ ሳይያዝ በመቅረቱ የተበላሸውና በ1851 እ.ኃ.ዘ.አ. በአንድ የዋልዳ ጠንቋይ እጅ ያየው ነው።

ኹለተኛው ቅጂ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ብቻ የያዘ መጽሐፍ (ዲ አባዲ 234) የተቀዳበት ብራና ነው። ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ በእጁ ገልብጦ በጻፈውና ወደ አንቷን ዲ አባዲ በፖስታ በላከው ዲ አባዲ 234 መጽሐፍ ውስጥ ራሱ ኡርቢኖ በ28 የካቲት 1853 ያሰፈረው ማስታወሻ አለ። በዚኽ ማስታወሻ ውስጥ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ እንደጻፈው ይኽኛው ቅጂ ከወታደር ልጆች አንዱ ከደምቢያ ዘመቻ በመመለስ ሳለ የዳዊት መዝሙር መግዛት ይፈልግ እንደኾነ ጠይቆት እሱም መጽሐፉን አይቶ ምን እንደኾነ ካወቀ በኋላ የገዛውና

በደህና ኹኔታ የነበረው ባለ 104 ገጾች መጽሐፍ ነው። ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ በ10 የካቲት 1853 ወደ አንቷን ዲ አባዲ በጻፈለት ደብዳቤም ይኽ መጽሐፍ ማግኘቱን ነግሮታል። በዚኽ ደብዳቤ እንደተገለጸውም ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ራሱ ለመላክ እንዲመቸው ስስ ወረቀት፣ ጠቃቅን ፊደላትና የአውሮፓ የብዕር ቀለም ተጠቅሞ ዲ አባዲ 234 በእጁ ገልብጦ የቀዳው ከዚኽ ቅጂ ነው።

በተጨማሪም ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ በ10 የካቲት 1853 ወደ አንቷን ዲ አባዲ በጻፈለት ደብዳቤ እንዳሰፈረው ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ከግእዝ ወደ ፈረንሳይኛ ቋንቋ ለመጀመሪያ ጊዜ (በራሱ በጁስቶ ዳ ኡርቢኖ) የተተረጎመውም ከዚኽ (ኹለተኛው) ቅጂ ነው (Wion 2012)።

ሶስተኛው ቅጂ ሐተታ ወልደ-ሕይወት ጭምር የያዘ መጽሐፍ (ዲ አባዲ 215) የተቀዳበት ብራና ነው። ዲ አባዲ 215 ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ በፋሲካ-ትንሳኤ 1854 እ.ጎ.ዘ.አ. በጻፈው ደብዳቤ እንደገለጸው በአንድ ታለሪ የገዛውና አመቺ ዕድል ሲገጥመው ራሱ ካሰናዳቸው የግእዝ-ፈረንሳይኛ መዝገበ ቃላት እና ሌላ የሰዋስው መጽሐፍ ጋር ለአንቷን ዲ አባዲ እንደሚልክለት ቃል የገባለት መጽሐፍ ነው። ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ዲ አባዲ 215 መጽሐፍን የተቀዳበት ቅጂ ያገኘበት መንገድም ራሱ በእጁ ገልብጦ በጻፈውና ወደ አንቷን ዲ አባዲ በፖስታ በላከው ዲ አባዲ 234 መጽሐፍ ውስጥ በ28 የካቲት 1853 ያሰፈረው ማስታወሻ ውስጥ ገልጾታል። በዚኽ ማስታወሻ እንደመዘገበው መጽሐፉን ያገኘው ወላጆቹ በጣና ሃይቅ ደሴቶች የሚኖሩ የደብረ-ታቦር ደብተራ ወይም ምሁር በትንሳኤ ሳምንት ከጣና ደሴቶች ሲመለስ መጽሐፉ ይዞለት እንደሚመጣና እንዲጠብቀው ቃል በገባለት መሰረት ነው። ይኽ እውነታ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ለ ዲ አባዲ በ10 የካቲት 1853 በጻፈው ደብዳቤም ደግሞ አስፍሮታል። በዚኽ ደብዳቤ እንደተጻፈው ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ዲ አባዲ 215 መጽሐፍ የተቀዳበት ቅጂ ያገኘበት መንገድ ያ ወላጆቹ በጣና ሃይቅ ደሴቶች የሚኖሩ የደብረ-ታቦር ደብተራ ወይም ምሁር መጽሐፉ መኖሩን አይቶት ስለነበረ ቅጂውን ቀድቶ በአንድ ታለሪ ዋጋ እንደሚያመጣለት በገለጸበት ተመሳሳይ አኳኋን ነው (Wion 2012) ።

እነዚኽ ከላይ የተገለጹ ሶስት የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ቅጂዎች እና ከቅጂዎቹ አንዱ በመውሰድ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ (ወደ ፈረንሳይኛ) የተረጎመው ስራ የት እንደገቡ ወይ እንዳሉ አይታወቁም፤ ለማግኘት የተደረገ ጥረት ግን አይጠፉም (Wion 2012)።

በተመሳሳይ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ በ 9 መጋቢት 1852 እ.ጎ.ዘ.አ. በጻፈው ደብዳቤ እንዳሰፈረው የቅርጣግና ሌሊቶች የግእዝ ትርጉም መጻሕፍት ብዛት ቢያንስ 4 እና 5 ይኾኑ እንደነበር አመልክቷል። እስካኹን ማግኘት የተቻለው ግን በቫቲካን በመለያ ቁጥር 165 የሚገኝ አንዱን ቅጂ ብቻ ነው። በተጨማሪ ቢያንስ ኹለት የቅርጣግና

ሌሊቶች የአማርኛ ትርጉሞች ስላሉ ኹለት እና ከዛ በላይ የግእዝ ቅጂዎች መኖራቸው መቀበል የሚያዳግት ሐቅ አይደለም።

ታዲያ እነዚኽ የቫቲካኑ መጽሐፍ ቅጂዎች ወደ የት ጠፉ? እነዚኽ የቅርብ ዘመን መጻሕፍት የጠፉበት የኢትዮጵያ የአዙሪት ፖለቲካ-ኢክኖሚ ዓውድ እና የመጠፋፋት ጦርነት ታሪክ ከተቀበልን (የሩቅ ዘመን) መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ቅጂዎች ያልተገኙበት ምክንያትም በሚገባ እንረዳለን። በተጨማሪም ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ መጽሐፍ መኖሩን ያወቀበት፣ ያፈላለገበት እና ያገኘበት መንገድ በግልጽ ጽፎ አቆይቶልናል። ታሪኩም ወጥ እና በማስረጃ የተደገፈ በመኾኑ ደግሞ ተአማኒነቱ ፈጽሞ አያጠራጥርም። በመኾኑ ራሱ በተወልን ማስረጃ ሊደገፍ የሚችለውን ቃሉ ወስደን ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ እንዳልኾነ ልንቀበል ግድ ያስፈልጋል (Sumner 1976) ።

ክፍል ሶስት፤ ማጠቃለያ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስትያን ትምህርት በአራት ዓበይት ምዕራፎች ይከፈላል። እነሱም የንባብ ክፍል ፣ የዜማ ክፍል (ቅዳሴና አቋቋም ጨምሮ)፣ የቅኔ ክፍል፣ የመጻሕፍት ትርጓሜ ክፍል (የባሕረ ሓሳብ ትምህርት ጨምሮ) እንደኾኑም ይታወቃል። በዚኽ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን ሥርዓተ ትምህርት በወጥነት ለንባብ፣ ለዜማ፣ ለቅኔና ሰዋስው፣ ለትርጓሜ መጻሕፍት ማስተማርያነት የሚውል መጽሐፍ ደግሞ የዳዊት መዝሙር ብቻ ነው።

በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ምዕራፍ 1 እንደተገለጸው ዘርዐ-ያዕቆብ የዳዊት መዝሙር (ንባብ) አጥንተዋል። ለሦሥት ወራት ያክልም ዜማ ተምረዋል። ቀጥሎ ለአራት ዓመታት ቅኔና ሰዋስው አጥንተዋል። ለዓስር ዓመት ደግሞ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ ተምረዋል። ከዚኽ በኋላ በአክሱም መጻሕፍትን ለአራት ዓመት ያህል አስተምረዋል። በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ምዕራፍ 11 ደግሞ ዘርዐ-ያዕቆብ የዳዊት መዝሙር መጽሐፍ እንደጻፈና ለሕጻናት የዳዊት መዝሙር ንባብ እንዳስተማረ ተመላክተዋል። ይኽ የሕይወት ታሪክና ጎዞ በራሱ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ ኢትዮጵያውነት ይመሰክራል።

የዳዊት መዝሙር በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ የተጠቀሰበት መንገድ፣ በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ የሚገኙ የዳዊት መዝሙር ንባቦች የቀረቡበት ዓውድ፣ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ በመጽሐፉ የተገለጸበት ምስል እና በመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ የሚገኙ የዳዊት መዝሙር ንባቦች ምንጮች ስንመረምራቸው ደግሞ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ የዳዊት መዝሙር ልዩ ዕውቀት፣ ፍቅር እና ክብር ከዚኽ

ከተገለጸው የኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ትምህርት፣ ባህል፣ ልምድና እና ኑሮ በእጅጉ እንደሚቆራኝ ያሳያሉ።

የጁስቶ ዳ ኡርቢኖ ኹሉም ስራዎች ስናይም የነበረው የዳዊት መዝሙር ዕውቀት ወይም ለየዳዊት መዝሙር በስራዎቹ የሰጠው ትኩረት አናሳ እንደኾነ እናያለን። ይኽ ባህርይ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ መለያ አይደለም። ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ በእጁ በገለበጠው ዲ አባዲ 234 ያሉ የዳዊት መዝሙር ምልክቶችም ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ አራሚ እንጂ ጸሐፊ እንደኾነ አያመለክቱም። በመኾኑም ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ መኖሩን ያወቀበት፣ ያፈላለገበት እና ያገኘበት መንገድ አስመልክቶ በግልጽ ጽፎ ባቆየልን ወጥ እና በማስረጃ የተደገፈ ታሪክ ላይ ተመስርተን ስንመረምር የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ጸሐፊ ኢትዮጵያውነት ልንቀበለው የሚገባ ሐቅ ኾኖ እናገኘዋለን።

ዋቢ መጻሕፍት

Brooh Asmare. 2022. The authenticity of the hatata from the perspective of the cultural history of Ethiopia. In *Philiminality*.

D'Abbadie, Antoine. 1859. Catalogue raisonné de manuscrits éthiopiens. Paris: Imprimerie Imperiale.

Dawit Worku Kidane. 2012. *The Ethics of Zara Yaeqob: a reply to the historical and religious violence in the seventeenth century Ethiopia*. Edited by Pontificia Universita Gregoriana. Vol. 30, *Filosofia*. Roma: Gregorian and Biblical Press.

Ethiop_Abb_215. ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ Bibliothèque nationale de France.

Ethiop_Abb_216. Abrege de grammaire ethiopienne, ecrit en Ethiopie, par J.C. d'Urbino, en 1850-1854. Bibliothèque nationale de France.

Ethiop_Abb_217. Dictionnaire ethiopien (francais-amarinna compile en Ethiopie par J.C. d'Urbin, en 1850-55. Bibliothèque nationale de France.

Ethiop_Abb_234. መጽሐ ፈ ሐተታ ዘዘርአያዕቆብ Bibliothèque nationale de France.

Fasil Merawi. 2017. "Zera Yacob's Hatata and the vitality of an Indigenous Ethiopian Philosophy." *EJSS* no. 3 (2).

Fasil Merawi. 2022. Examining the hatetas as a foundation of Ethiopian philosophy. In *Philiminality*.

Fasil Merawi and Kenaw Setargew. 2019. "Is there an Ethiopian Philosophy? Rereading the Hatetas of Zara Yaecob and Walda Hewat in the Context of Knowledge Production." *Ethiopian Journal of the Social Sciences and Humanities (EJOSSAH)* no. 15 (1-Special Issue). doi: 10.4314/ejossah.v15i1.6.

Getachew Haile. 2017. "The Discourse of Warqe." In *Ethiopian Studies In Honour of Amha Asfaw*. New York.

Graness, Anke. 2022. Of foreigners and misinterpretations. In *Philiminality*.

Kropp, Manfred. 1992. A statistic and stylistic approach for resolvig the problem of authorship of hatata Zara Yaqob.

Lee, Ralph. 2022. Reflections on translating the hatata into English. In *Philiminality*.

Lee, Ralph, Mehari Zemelak Worku, and Wendy Laura Belcher. 2024. *Two Texts of Seventeenth-Century African Philosophy from Ethiopia about Reason, the Creator, and Our Ethical Responsibilities*. Translated by Ralph Lee, Mehari Zemelak Worku and Wendy Laura Belcher.

Luam Tesfalidet. 2007. *Rezeptionsgeschichte der Ḥatäta Zär'a Yaʿəqobs und Wäldä Ḥəywät*, Universität Hamburg, Hamburg.

Marenbon, John. 2022. Does it matter who wrote it? Zera Yacob, forgery and pseudonymity in the history of philosophy. In *Philiminality*.

Mbodj, Aissatou, and Anais Wion. 2013. "The history of a genuine fake philosophical treatise (hatata Zara Yaeqob and hatata Walda Heywat) (Introduction: Investigating an Investigation)." *Afriques, debates and readings*.

Smith, Justin E.H. 2022. Assessing the evidence for Zera Yacob's authenticity from the point of view of the history of philosophy. In *Philiminality*.

Srivastava, Neelam. 2022. Italian colonialism and orientalism in ethiopia. In *Philiminality*.

Sumner, Claude. 1976. *The Treatise of Zar'a Ya'aqob and of Walda Heywat Text and Authorship*. Vol. 2, *Ethiopian Philosphy*. Addis Ababa: Commericial Printing Press.

Teshome Abera Tesema. 2019. "Philosophy in Zerayacob's Hatata." *International Journal of Multidisciplinary Research and Development* no. 6 (12):64-67.

Teshome Abera Tesema. 2022. Zara Yacob's Hatata: its historical and social reality. In *Philiminality*.

Wion, Anais. 2012. "Lettres du R. P. Juste d'Urbin à Antoine d'Abbadie Manuscrit BnF NAF 23852, fol. 3- 128v."

Wion, Anais. 2013a. "The history of a genuine fake philosophical treatise (hatata Zara Yaeqob and hatata Walda Heywat). Episode 2: the time of debunking, the time in the wilderness (from 1916 to the1950s)." *Afriques, debates and readings*.

Wion, Anais. 2013b. "The History of a Genuine Fake Philosophical Treatise (Ḥatatā Zar'a Yā'eqob and Ḥatatā Walda Ḥeywat). Episode 1: The Time of Discovery. From Being Part of a Collection to Becoming a Scholarly Publication (1852-1904)." doi: 10.4000/afriques.3178.

በላይ መኰንን እና መኰንን ኤፍሬም፥ 2013፥ *ምዕራፍ ዘቅዱስ ያሬድ ፤ ምስለ መልክዐ ያሬድ፥ ምቅናይ ዘሕንጸተ ቤተክርስቲያን ወዜና ሕይወት ዘቅዱስ ያሬድ*፥ 2ኛ እትም፥ አዲስ አበባ

በእምነት ገብረአምላክ፥ "ሐተታ ዘርአ ያዕቆብና አባ ጁስቶ ዳ ኡርቢኖ የተላላኪው የካርሎ ኮንቲ ሮሲኒ ማስታወሻ"

ብሩህ አለምነህ፥ 2011፥ *የዘርዓ ያዕቆብና የወልደ ሕይወት ሐተታዎች ትንታኔ፤ ታሪክ ሃይማኖት፣ ፍልስፍና ሀገራዊ ቁጭት የተዋኻዱበት የኢትዮጵያ ፍልስፍና*፥ 5ኛ እትም፥ አዲስ አበባ

ንጉሥ ካሕሳይ፥ 2016፥ *ነገረ ወርቅየ፤መጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ አክሱማዊ ከነእርማቱ (ISBN: 978-99990-0-639-2)*

ዓለማየሁ ሞገስ፥ 1961፥ *ሐተታ ዘዘርዓ ያዕቆብ ኢትዮጵያዊ ፈላስፋ፤ ዘርአ ያዕቆብ ኢትዮጵያዊው መሆኑን ለማስረዳት ለቢኤ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት*፥ አዲስ አበባ::

ያሬድ ፈንታ ወልደዮሐንስ፥ 2007፥ *ሐተታ ዘርዐ ያዕቆብ ወሐተታ ወልደ ሕይወት፤ የኢትዮጵያ ፍልስፍና*፥ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ሐላፍነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር

ዳንኤል ክብረት፥ 2011፥ "የሌለውን ፈላስፋ ፍለጋ" በ *የሌለውን ፈላስፋ ፍለጋ* እና ሌሎች፥ አዲስ አበባ፥ አማዮስ ሕትመትና ጠቅላላ ንግድ ሥራ ሐላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር

ዳዊት ግርማ፥ 2019፥ "እንስታዊነት በኢትዮጵያ ፍልስፍና፤ ሐተታ ዘርአ ያዕቆብና ሐተታ ወልደ ሕይወት እንደማሳያ"፥ *ERJSSH* no. 6 (1)

ጌታቸው ኃይሌ፥ 2006፥ ሐተታ ዘዘርአ ያዕቆብ በሚ ባል ስም የሚ ታወቀው የወርቁ የሕይወት ታሪክ፥ ኮሌጅቪል (ሚ ኒሶታ)

ጌታቸው ኃይሌ፥ 2012፥ *ስግዕዝ ሥነ-ጽሑፍ ጋር ብዙ ሰፍታ ቆይታ*፥ አዲስ አበባ፥ ጃጃው አሳታሚ ዎችና ዲቨሎፐርስ ሐላፍነቱ የተወሰነ የግል ማ ሕበር

ጥዑመልሳን ካሳ፥ 1981፥ *ያሬድና ዜማው*፥ አዲስ አበባ፥ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት::

[1] አምሳሉ አክሊሉ፥ ዘርዐ-ያዕቆብ ፈላስፋው፥ ታሪክ መጽሔት (Tarik, gazette d'information archeology, no. 1 (1963), pp. 11-13)
[2] የ ዲ አባዲ 215 የዘመንፈስ-ቅዱስ አብርሃ ትርጉም ስራ
[3]

የዳዊት መዝሙር ምዕራፍ ጥቅሶች (ሰባ ሊቃውንት)	ድግግሞሽ	የዳዊት መዝሙር ምዕራፍ ጥቅሶች (ዕብራይስጥ)	ድግግሞሽ
2	1	2	1
8	1	8	1
9	2	9	1
11	1	10	1
12	1	12	1
13	1	13	1
24	1	14	1
27	1	25	1
30	3	28	1
32	1	31	3
33	1	33	1
34	1	34	1
35	1	35	1
36	3	36	1
39	2	37	3
40	1	40	2
50	4	41	1
54	2	51	4
60	1	55	2
61	2	61	1
65	1	62	2
70	1	66	1
72	3	71	1
83	1	73	3
85	1	84	1

93	1	86	1
95	1	94	1
96	1	96	1
108	2	97	1
114	1	109	2
115	1	116	2
117	1	118	1
118	6	119	6
127	1	128	1
137	1	138	1
138	1	139	1
140	1	141	1
142	2	143	2
147	1	147	1
ብዛት	**59**	**ብዛት**	**59**

[4] ዲ አባዲ 215/234 ምዕራፍ 1፣ (ዕብራይስጥ) ዳዊት መዝሙር 36፥9
[5] ዲ አባዲ 215 ምዕራፍ 3፣ (ዕብራይስጥ) ዳዊት መዝሙር 99፥3/106፥47
[6] ዲ አባዲ 215 ምዕራፍ 3፣ (ዕብራይስጥ) ዳዊት መዝሙር 102፥27
[7] ዲ አባዲ 215/234 ምዕራፍ 3፣ (ዕብራይስጥ) ዳዊት መዝሙር 4፥3/55፥16
[8] ዲ አባዲ 215/234 ምዕራፍ 9፣ (ዕብራይስጥ) ዳዊት መዝሙር 22፥11
[9] ዲ አባዲ 215/234 ምዕራፍ 10፣ (ዕብራይስጥ) ዳዊት መዝሙር 25፥18
[10] ዲ አባዲ 215/234 ምዕራፍ 10፣ (ዕብራይስጥ) ዳዊት መዝሙር 92፥5
[11] ዲ አባዲ 215/234 ምዕራፍ 11፣ (ዕብራይስጥ) ዳዊት መዝሙር 128፥2
[12] ዲ አባዲ 215/234 ምዕራፍ 13፣ (ዕብራይስጥ) ዳዊት መዝሙር 35፥12/38፥20
[13] ዲ አባዲ 215/234 ምዕራፍ 15፣ (ዕብራይስጥ) ዳዊት መዝሙር 41፥2
[14] ዲ አባዲ 215 ምዕራፍ 13፣ (ዕብራይስጥ) ዳዊት መዝሙር 14፥4/53፥4
[15] ዲ አባዲ 215/234 ምዕራፍ 6፣ (ዕብራይስጥ) ዳዊት መዝሙር 14፥5/140፥3
[16] ዲ አባዲ 215/234 ምዕራፍ 13፥ (ዕብራይስጥ) ዳዊት መዝሙር 79፥12
[17] ዲ አባዲ 215/234 ምዕራፍ 13፣ (ዕብራይስጥ) ዳዊት መዝሙር 14፥4/53፥4
[18] ምዕራፍ 1 ገጽ 1 የግራ ቅጠል መስመር 5
[19] ምዕራፍ 11 ገጽ 24 የቀኝ ቅጠል መስመር 1፣ ምዕራፍ 14 ገጽ 28 የግራ ቅጠል መስመር 7
[20] ምዕራፍ 3 ገጽ 4 የግራ ቅጠል መስመር 8 እና 10፣ ምዕራፍ 4 ገጽ 6 የቀኝ ቅጠል መስመር 22፣ ምዕራፍ 4 ገጽ 6 የግራ ቅጠል መስመር 6 ፣ምዕራፍ 6 ገጽ 12 የቀኝ ቅጠል መስመር 15 እና ምዕራፍ 9 ገጽ 19 የግራ ቅጠል መስመር 20
[21] ምዕራፍ 2 ገጽ 3 የቀኝ ቅጠል መስመር 10፣ ምዕራፍ 2 ገጽ 3 የግራ ቅጠል መስመር 16፣ ምዕራፍ 9 ገጽ 18 የግራ ቅጠል መስመር 5፣ ምዕራፍ 9 ገጽ 19 የግራ ቅጠል መስመር 17፣ ምዕራፍ 10 ገጽ 20 የግራ ቅጠል መስመር 16 እና ምዕራፍ 12 ገጽ 26 የቀኝ ቅጠል መስመር 14
[22] ምዕራፍ 11 ገጽ 23 የቀኝ ቅጠል መስመር 12 ፣ ምዕራፍ 11 ገጽ 23 የግራ ቅጠል 5፣ 11 እና 15

[23] ምዕራፍ 5 ገጽ 8 የግራ ቅጠል መስመር 4-7
[24] ምዕራፍ 5 ገጽ 9 የቀኝ ቅጠል መስመር 8-13
[25] ምዕራፍ 5 ገጽ 9 የግራ ቅጠል መስመር 1-4
[26] ምዕራፍ 5 ገጽ 10 የቀኝ ቅጠል መስመር 22-23 እና ምዕራፍ 5 ገጽ 10 የግራ ቅጠል መስመር 1-2
[27] ምዕራፍ 5 ገጽ 10 የግራ ቅጠል መስመር 11-15
[28] ምዕራፍ 9 ገጽ 19 የግራ ቅጠል መስመር 19-22
[29] ምዕራፍ 5 ገጽ 9 የግራ ቅጠል መስመር 5-10
[30] ምዕራፍ 4 ገጽ 8 የቀኝ ቅጠል መስመር 10-16
[31] ምዕራፍ 9 ገጽ 19 የግራ ቅጠል መስመር 15-19
[32] ምዕራፍ 2 ገጽ 3 የቀኝ ቅጠል መስመር 8-12
[33] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 37፥11
[34] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 78፥2
[35] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 8፥2
[36] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 48፥2
[37] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 110፥1
[38] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 98፥1፤ 107፥8-9
[39] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 118፥26
[40] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 118፥26
[41] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 118፥22
[42] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 31፥5
[43] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 69፥9
[44] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 82፥6-7
[45] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 69፥4
[46] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 69፥25
[47] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 16፥8-11
[48] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 118፥22
[49] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 2፥1-2
[50] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 78፥20
[51] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 51፥4
[52] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 32፥1-2
[53] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 69፥22-23
[54] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 18፥49
[55] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 2፥7
[56] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 102፤25-27
[57] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 8፥4-6
[58] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 22፥22
[59] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 95፥9-11
[60] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 95፥8
[61] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 95፥8
[62] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 110፥4
[63] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 40፥6-8
[64] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 118፥6-9
[65] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 34፥12-16
[66] (ዕብራይስጥ) የዳዊት መዝሙር 2፥9
[67] ዲ አባዲ 215/234 ምዕራፍ 5፤ (ዕብራይስጥ) ዳዊት መዝሙር 5፥4
[68] ዲ አባዲ 234 ምዕራፍ 9/ ዲ አባዲ 215/234 ምዕራፍ 10፤(ዕብራይስጥ) ዳዊት መዝሙር 23፥6/27፥4
[69] ዲ አባዲ 215/234 ምዕራፍ 6፤ (ዕብራይስጥ) ዳዊት መዝሙር 145፥14
[70] የሰባ ሊቃውንትና የዕብራይስጥ እትሞች የዳዊት መዝሙር ምዕራፍ አከፋፈል የተለያየ ነው። የሚታረቁትም ቀጥሎ በተገለጸው መልኩ ነው።

የዳዊት መዝሙር ምዕራፍ (ሰባ ሊቃውንት)	የዳዊት መዝሙር ምዕራፍ (ዕብራይስጥ)
1-8	1-8
9፥1-21	9
9፥22-39	10
10-112	11-113
113	114፥1-8
113	115፥9-26
114	116፥1-9
115	116፥10-19
116-145	117-146
146	147፥1-11
147	147፥12-20
148-150	148-150
151	

[71] **የመጽሐፈ ሐተታ ዘርዐ-ያዕቆብ ኹለቱ ቅጂዎች ጨምሮ**
[72] Spettatore egiziano Anno 1 No 18 29 January 1856, Anno 1 No 19 8 February 1856, Spettatore egiziano Anno 1 No 20 18 February 1856
[73] Vatican Archivio storico de propaganda fide - congress Africa Centrale Etiopia vol. 4 (1841-47), 5 (1848-57), and 6(1858-60) Cogressi egittovol.19 (1854-61)
[74] Ms. 167
[75] Rome Biblioteca delia Societa Geografica Italiana
[76] Rome Bibliotecanazionale Vittorio Emanuele
[77] Orientale 134
[78] MS. d'Abbadie 216. Paris, Bibliotheque nationale. Abrege de grammaire ethiopienne, ecrit en Ethiopie, par J.C. d'Urbino, en 1850-1854